https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፹፪
አዲስ አበባ ነሐሴ ፮ ቀን ፳፻፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.82
ADDIS ABABA 12th August, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፰/፳፻፲፩ ዓ.ም

የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ……...ገጽ ፲፩ሺ፭፻፴፰

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፰/፳፻፲፩

## ስለ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የወጣ አዋጅ

የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆናቸውን በመገንዘብ፣

መንግሥት የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ለማሻሻል የቴሌኮሙኒኬሽን የገበያ ሥርዓቱን እንደገና ለማደራጀትና በውድድር ላይ የተመሠረተ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት እንዲኖር የወሰነ በመሆኑ፤

መንግሥት የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያውን እንደገና ለማዋቀርና በቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውድድርን ለማስፈን ያስቀመጠውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማሳካት ነፃ፣ ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፰ / ፳፻፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል.

## Content

Proclamation No.1148/2019

Communications Service Proclamation...Page 11,538

## PROCLAMATION NO. 1148/2019

## A PROCLAMATION FOR THE COMMUNICATIONS SERVICE

WHEREAS, Communication Services serves an essential function in the economic and social development of the Country;

WHEREAS, the Government has decided to restructure the telecommunications market and introduce competition in the provision of telecommunications service in order to enhance the economic and social development of the Country;

WHEREAS, the establishment of an independent, transparent, and accountable Regulatory Authority is necessary to achieve the Government's policy of restructuring the telecommunications market and introducing competition;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE
## *GENERAL*

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Communications Service Proclamation No. 1148/2019."

https://chilot.me



## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "ይግባኝ ሰሚ አካል" ማለት በባለሥልጣኑ የተሰጠ ውሳኔ ላይ የቀረበ ይግባኝ ለማየትና ለመወሰን ዓላማ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ አካል ነው፤

፪/ "የሥራ አመራር ቦርድ" ማለት የባለሥልጣኑ የበላይ አስተዳዳሪ አካል ማለት ነው፤

፫/ "ብሮድካስተር" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የብሮድካስት አገልግሎት እንዲሰጥ በኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጠው አካል ነው፣

፬/ "ብሮድካስቲንግ" ማለት የሬዲዮ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ለሕዝብ በድምፅና በምስል ማስተላለፍ እና ማሰራጨት ነው፤

፭/ "የኮሙኒኬሽን አገልግሎት" ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን ማስተላለፊያ መስመር በመጠቀም የድምፅ፣ የምስል ወይም የዳታ እና ፖስታን በመጠቀም ቁሳዊ ይዘት ያለው መልዕክት የማሰራጨት ወይም የመቀበል አገልግሎት ለሕዝብ መስጠት ሲሆን የብሮድካስቲንግ አገልግሎትን ግን አያካትትም፤

፮/ "የመረጃ አገልግሎት" ማለት መረጃን ለማመንጨት፣ ለማግኘት፣ ለማከማቸት፣ ለመለወጥ፣ ለማቀናበር፣ ለመጠቀም ወይም ቴሌኮሙኒኬሽንን በመጠቀም መረጃ እንዲገኝ ለማድረግ የሚያስችል አቅም የማቅረብ እና የኤሌክትሮኒክ ህትመትን የሚያካትት ሲሆን፣ ማንኛውንም እንዲህ ዓይነት ችሎታ ለቴሌኮሙኒኬሽን ስርዓት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስተዳደር፣ ቁጥጥር ወይም አመራር መጠቀምን አያካትትም፤

፯/ "ኢንተርኮኔክሽን" ማለት የአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ከተመሳሳይ ወይም ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ጋር እንዲገናኙ ወይም በሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚሰጡ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያስችል በተመሳሳይ ወይም ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ጥቅም ላይ የዋሉ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ አካላዊ፣ ቴክኒካዊ እና ምክንያታዊ ግንኙነት ማለት ነው፡፡ አገልግሎቶች በተሳተፉ አካላት ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ተደራሽነት ባላቸው አካላት ሊቀርቡ ይችላሉ፤

## 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "Appeals Tribunal" means the body established by this Proclamation for the purpose of adjudicating appeals of Decisions of the Authority;

2/ "Board of Management" shall mean the Governing Board of the Authority;

3/ "Broadcaster" means an entity that is licensed by the Ethiopian Broadcasting Authority to provide broadcasting service within the territory of Ethiopia;

4/ "Broadcasting" means the emission and dissemination of radio or television programming intended for reception by the public;

5/ "Communications Service" means service offered to the public consisting of the dissemination or interchange of audio, video or data content using telecommunications media, and of physical content using postal service, but does not include broadcasting;

6/ "Information Service" means the offering of a capability for generating, acquiring, storing, transforming, processing, retrieving, utilizing, or making available information via telecommunications, and includes electronic publishing, but does not include any use of any such capability for the management, control, or operation of a telecommunications system or the management of a telecommunications service;

7/ "Interconnection" means the physical, technical and logical linking of the Telecommunications Networks used by the same or a different Telecommunications Operator in order to allow the users of one telecommunications operator to communicate with users of the same or another Telecommunications Operator, or to access services provided by another Telecommunications Operator. services may be provided by the persons involved or by other persons who have access to the Telecommunications Network;

https://chilot.me



፰/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፤

፱/ "ባለሥልጣን" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፫ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባለሥልጣን ነው፤

፲/ "የህዝብ ውይይት" ማለት ባለሥልጣኑ በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ ባሉ ጉዳዮች ላይ የህብረተሰቡን አስተያየት የሚሰማበት ሂደት ነው፤

፲፩/ "ጉልህ የገበያ ድርሻ" ማለት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያዎችን ወይም በገበያው ውስጥ ያለውን የገበያ ድርሻ አቅም በመጠቀም በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዋጋ ወይም አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የማድረግ ችሎታ ነው፤

፲፪/ "የባለድርሻ አካላት ምክክር" ማለት ባለሥልጣኑ በማንኛውም ወገን ወይም የሕዝብ ጥቅም መብት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር በሚችል በማንኛውም በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ ባለ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጥበት ግልፅ ሂደት ነው፤

፲፫/ "ታሪፍ" ማለት በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የሚጠየቅ ማንኛውም ክፍያ፣ ዋጋ ወይም ተመን ነው፤

፲፬/ "ቴሌኮሙኒኬሽን" ማለት ድምፅ፣ ምልክት፣ ጽሁፍ፣ ምስል ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሌላ መረጃ በኤሌክትሮመግነጢሳዊ ኃይል አማካኝነት በስልክ ሽቦ፣ በሬዲዮ፣ በብርሃን ሞገድ ወይም በሌላ ኤሌክትሮመግነጢሳዊ ስልት ማሰራጨት፣ ማስተላለፍ ወይም መቀበል ሲሆን በማሰራጨቱ፣ በማስተላለፉ ወይም በመቀበሉ ሂደት ድምፁ፣ ምልክቱ፣ ጽሑፉ፣ ምስሉ ወይም መረጃው እንደገና መደራጀት ወይም በሌላ መንገድ ለውጥ የተደረገበት መሆኑ ልዩነት አያመጣም፤

፲፭/ "የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያ" ማለት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የዋለ ወይም ሊውል የታቀደ ማንኛውም መሣሪያ ሲሆን የመሣሪያውን ተገጣሚ አካል ይጨምራል፡፡

፲፮/ "የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር" ማለት ከቴሌኮሙኒኬሽን ስርዓት ጋር ለተያያዘ አገልግሎት የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ የስልክ ሽቦ፣ ኬብል፣ ማማ፣ አንቴና፣ ምሰሶ ወይም ማናቸውም ሌላ መሣሪያ ነው፤

፲፯/ "የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ" ማለት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚውሉ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሮች እና ተዛማጅ የማዞሪያ ሥርዓቶች ስብስብ ነው፤

8/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Innovation and Technology;

9/ "Authority" shall mean the Ethiopian Communications Authority established under Article 3 of this proclamation

10/ "Public Hearing" means the process by which the Authority may solicit views of members of the public on a matter within the Authority's jurisdiction.

11/ "Significant Market Power" means the ability to materially affect the price or supply in the relevant market for Communications Service as a result of either control over essential facilities or use of a Person's position in the market;

12/ "Stakeholder Consultation" means the transparent process by which the Authority shall take action in any matter within its jurisdiction that may affect the rights of any party or the public interest.

13/ "Tariff" means any charge, price, or levy and underlying terms and conditions imposed by a Telecommunications Operator for a telecommunications service.

14/ "Telecommunications" means the emission, transmission, or reception, through the agency of electricity or electromagnetism, of any sounds, signs, signals, writing, images or intelligence of any nature by wire, radio, optical or electromagnetic systems, whether or not such sounds, signs, signals, writing, images or intelligence have been subjected to rearrangement, computation or other processes by any means in the course of their transmission, emission, or reception;

15/ "Telecommunications Equipment" means any appliance, apparatus, or accessory used or intended to be used for telecommunications services;

16/ "Telecommunications Line" means any wire, cable, tower, antenna, pole or any other equipment used or intended to be used in connection with a telecommunications system;

17/ "Telecommunications Network" means the collection of Telecommunications lines and associated switching systems that is used for the provision of telecommunications service;

https://chilot.me



፲፰/ "የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር" ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት በዚህ አዋጅ መሠረት በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ነው፣

፲፱/ "የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት" ማለት ፈቃድ በተሰጠው አካል በቀጥታ ለሕዝብ ወይም ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የሚሰጥ የቴሌኮሙኒኬሽን ማስተላለፍ አገልግሎት ነው፤

፳/ "ሁሉን አቀፍ ተደራሽነት" ማለት በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ሳይገደብ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን የጥራት ደረጃ የጠበቀ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ማዳረስ ነው፤

፳፩/ "ኮሎኬሽን" ማለት አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለአገልግሎት አቅርቦት የሚጠቀምባቸውን የኔትወርክ መሣሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የሌላኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኔትወርክ መሣሪያዎች ወይም ሥርዓቶች የተገጠሙበት ስፍራ ላይ በሁለቱ መካከል በሚደረሰው ስምምነት መሠረት ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ በአንድ ላይ ማስቀመጥ ነው፤

፳፪/ "ሲም ካርድ" ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንበኛ አገልግሎት ለማግኘት ከሚጠቀምበት የሞባይል ስልክ ቀፎ ወይም ሌላ መሣሪያ ጋር ተገጥሞ ከቴሌኮሙኒኬሽን ሥርዓቱ ጋር በመገናኘት ደንበኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ግንኙነት እንዲያደርግ እና እንዲቀበል እንዲሁም የቴሌኮሙኒኬሽን ሥርዓቱን የደንበኛውን ማንነት እና መረጃ ለይቶ እንዲያውቅ የሚያስችል የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንበኛ ማንነት መለያ ነው፤

፳፫/ "ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር እቅድ" ማለት ከቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅና የሚተዳደር የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር እቅድ ነው፤

፳፬/ "የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም" ማለት ከ፫ ኪሎ ኸርዝ እስከ ፫፻ ጊጋ ኸርዝ የሚሸፍን የፍሪኩዌንሲ ኤሌክትሮመግነጢሳዊ ሞገድ ነው፤

፳፭/ "ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ድልድል እቅድ" ማለት ከሬዲዮ ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል በባለሥልጣኑ የሚዘጋጅና የሚተዳደር የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም እቅድ ነው፤

18/ "Telecommunications Operator" means an entity authorized by the Authority pursuant to this Proclamation to provide telecommunications service;

19/ "Telecommunications Service" means the provision by a licensee of the conveyance of Telecommunications directly to the public or to Telecommunications Operators.

20/ "Universal Access" means the availability to all users, regardless of their geographic location, of Communications Services of a quality specified by the Authority and at suitable prices;

21/ "Collocation" means the placement of network equipment or systems which are used for service provision by a Telecommunications Operator together with network equipment or systems installed at premises of other Telecommunications Operator at technically feasible location on the basis of agreement reached between them;

22/ "SIM-card" means the Subscriber Identity Module which is an independent electronically-activated device designed for use in conjunction with a telecommunication apparatus to enable the user of the telecommunication apparatus to transmit and receive communications by providing access to telecommunication systems and enabling such telecommunication systems to identify the particular subscriber identity module and its installed information;

23/ "National Telecommunication Numbering Plan" shall mean the telecommunication numbering plan prepared and managed by the Authority for use in connection with the supply of telecommunications services in Ethiopia;

24/ "Radio Frequency Spectrum" shall mean electromagnetic waves of frequencies from 3 KHz to 300 GHz;

25/ "National Frequency Allocation Plan" means the radio frequency spectrum plan prepared and managed by the Authority for use in connection with the supply of Radio communication services in Ethiopia;

https://chilot.me



፳፮/ “ቁጥር ማዛወር” ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ደንበኞች በተመሳሳይ ቦታ ወይም ስፍራ የሚጠቀሙበትን የስልክ ቁጥር ሳይቀይሩ ከአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር መዛወር የሚችሉበት ሁኔታ ነው፤

፳፯/ “የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ” ማለት ለእያንዳንዱ ኮምፒዩተር ፣ ፕሪንተር ፣ ስዊች ፣ ራውተር ወይም ማንኛውም የኔትወርክ አካል የሆነ ሌላ መሣሪያ የሚሰጥ አግባብነት ያለው አሃዛዊ አድራሻ ነው፤

፳፰/ “የዶሜይን ስም” ማለት በአንድ ምድብ የሚካተት የኔትወርክ አካል አድራሻ መለያ ስም ነው፤

፳፱/ “የንጽጽር ችሎት” ማለት ለአንድ የተወሰነ ፈቃድ በርካታ አካላት በሚያመለክቱበት ጊዜ በላቀ ሁኔታ ለህዝብ ጥቅም የሚሰጠው አመልካች የሚመረጥበት አሰራር ወይም ዘዴ ነው፤

፴/ “የደንበኛ መገልገያ መሣሪያ” ማለት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩን ወይም የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጭውን መሣሪያ ሳይጨምር ደንበኛው በሚገኝበት ቦታ ወይም ስፍራ ተገጥሞ ወይም ደንበኛው ይዞት እየተንቀሳቀሰ የቴሌኮሙኒኬሽን ግንኙነት ለማድረግ፣ ለመቀበል የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው፤

፴፩/ “ነፃና ገለልተኛ” ማለት በአሰራር ተለይቶ የተቋቋመ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ከማንኛውም ወገን ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በግልፅነት እና በተጠያቂነት የሚፈፅምና ውሳኔ የሚሰጥ የመንግስት ተቋም ነው፤

፴፪/ “ኢንስፔክተር” ማለት ባለፈቃዶች ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን አክብረው መስራታቸውን የሚቆጣጠር በባለሥልጣኑ የሚመደብ ሰራተኛ ነው፤

፴፫/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፬/ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም በእኩል ያገለግላል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን

### ፫. መቋቋም

26/ "Number Portability" means the ability of users of telecommunications services to retain, at the same location, existing telecommunications numbers when switching from one telecommunications carrier to another;

27/ “Internet Protocol Address (IP address)” means a logical numeric address that is assigned to every single computer, printer, switch, router or any other device that is part of a TCP/IP-based network;

28/ “Domain Name” means the part of a network address that identifies it as belonging to a particular domain;

29/ “Comparative Hearing” means a procedure used to choose the applicant that best serves the public interest when multiple parties apply for a specific license;

30/ ‘‘Customer Premises Equipment" means equipment other than a Telecommunications Operator or Service Provider which is installed at the premises of a subscriber or used by a subscriber to make and receive telecommunications service;

31/ “Free and Independent” means a transparent and accountable government institution with distinct procedure and functions that performs its powers and duties vested in it under this proclamation being independent from influences of any other party;

32/ "Inspector" means a person assigned by the Authority, to supervise the proper observance of the provisions of this Proclamation and Regulations and Directives issued hereunder, by licensees;

33/ "Person" means a natural person or a juridical person;

34/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## THE COMMUNICATIONS AUTHORITY

### 3. Establishment

https://chilot.me



፩/ የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" ተብሎ የሚጠራ) ራሱን የቻለ፣ የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችል ነፃና ገለልተኛ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የባለሥልጣኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

## ፬. ዋና መስሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ጨምሮ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

## ፭. ዓላማ

የባለሥልጣኑ ዓላማ ተወዳዳሪ የገበያ ሥርዓትን በማበረታታት፣ የተጠቃሚዎችን ተደራሽነትና ፍላጎት ያሟላ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ እና ኢኮኖሚያዊ አቅምን ያገናዘበ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመላ ሀገሪቱ እንዲስፋፋ ማድረግ ይሆናል፡፡

## ፮. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመንግስት ፖሊሲ መሠረት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤

፪/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫/ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ ባለሥልጣኑን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በሕዝብ ጥያቄ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ያደርጋል፤

፬/ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ ለማከናወን ከማንኛውም ባለፈቃድ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር፣ የፖስታ ኦፕሬተር ወይም ብሮድካስተር አስፈላጊ የሆነ መረጃ መጠየቅ ይችላል፤

1/ The Ethiopian Communications Authority (hereinafter "the Authority") is hereby established to accomplish the mandate given to it by this Proclamation as an independent Federal Government Authority having its own legal personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Prime Minister .

## 4. Head Office

The Authority shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere including Dire Dawa City Administration as may be necessary.

## 5. Objectives

The objectives of the Authority shall be to promote the development of high quality, efficient, reliable and affordable communications service throughout the nation; to promote a competitive market for the achievement of these goals; and to promote accessibility and interests of consumers.

## 6. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the following powers and duties:

1/ To ensure that Communications Services are operated in a manner that will best serve and contribute to the Country's economic and social development, as per government policy;

2/ To implement policies for Communications Services;

3/ To hold Stakeholder Consultations on the matters committed to its discretion by this Proclamation, either on its own initiative or at the request of a member of the public;

4/ Require any licensee, Telecommunications Operator, Postal Operator or Broadcaster to provide information that reasonably finds to be necessary for the proper performance of its functions and the exercise of its powers under this Proclamation;

https://chilot.me



፭/ ደረጃዎችን ለማዘጋጀት ኃላፊነት ከተሰጣቸው ተቋማት እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጥበትን የቴክኒክ ደረጃ ይወስናል፤ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የተወሰነለትን የጥራት ደረጃ ጠብቆ መሰጠቱን ይቆጣጠራል፤

፮/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚጠየቀውን ታሪፍ ይቆጣጠራል፤

፯/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ ለሚሰማሩ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ፈቃድ ያሻሽላል፣ ያድሳል፣ ያግዳል ወይም ይሰርዛል፤

፰/ ከቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ጋር ተገናኝተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ዓይነት ይቆጣጠራል፤

፱/ በኢትዮጵያ ውስጥ ለንግድ፣ ለመንግሥት ፣ ለሃገር መከላከያ እና ለብሔራዊ ደህንነት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ ሚኒስቴሩን፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣንን እና በኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በበላይነት ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው ተቋምን ጨምሮ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፤

፲/ በዓለም አቀፍ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ደንቦች መሠረት በኢትዮጵያ የስፔስ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በበላይነት ለመምራት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ጋር በመመካከር ለሳተላይት ምህዋር ቦታ ምዝገባ ያመለክታል፣ ያሳውቃል፣ ያስተባብራል፤

፲፩/ ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ፕላን ያዘጋጃል፣ ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

፲፪/ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻና የሀገሪቱን የከፍተኛ ደረጃ ዶሜይን ጨምሮ የዶሜይን ስሞችን ይመድባል፣ ያስተዳድራል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤

5/ Specify technical standards for the provision of communications service, in cooperation with institutions mandated to set standards and other relevant bodies, and to ensure that communications services conform to the specified standards of quality;

6/ Regulate tariffs relating to communications service in accordance with the provisions of this Proclamation;

7/ Issue license and supervise operators of Communications Service and modify, renew, suspend or revoke licenses;

8/ Regulate types of Telecommunication Equipments that may be connected to a Telecommunication Network;

9/ Authorize and Supervise the use of the Radio Frequency spectrum in Ethiopia for commercial and government users including the military and intelligence services, in consultation with relevant parties, including the Ministry, the Ethiopian Broadcasting Authority and the organization mandated to lead Space Science and Technology activities in Ethiopia;

10/ Manage the notification, coordination and filing process of satellite orbital locations as per the framework of international radio frequency spectrum regulations, in consultation with the organization Authorized for Space Science and Technology activities in Ethiopia.

11/ Establish the national telecommunications numbering plan, allocate and administer numbers, and supervise efficient use thereof;

12/ Manage Internet Protocol addresses, domain names, including the Country Code top level domain for Ethiopia (.et), through allocating, assigning and supervising efficient use thereof;

https://chilot.me



፲፫/ በተለያዩ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጭዎች መካከል የሚኖረውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርኮች ኢንተርኮኔክሽን ይቆጣጠራል፤

፲፬/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት ያስጠብቃል፤

፲፭/ በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል እንዲሁም በተጠቃሚዎች እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ኦፕሬተሮች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ አለመግባባቶችን ይፈታል፤

፲፮/ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚኖራቸውን ተደራሽነት የሚያግዙትን ጨምሮ አዳዲስ የኮሙኒኬሽን ቴክኒኮች እና ቴክኖሎጂዎችን ለማልማት እና ለመጠቀም የሚያስችሉ ምርምሮችን ያበረታታል፣

፲፯/ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት መስጠት እና ማካሄድን በተመለከተ በፖሊሲና የሕግ ጉዳዮች ላይ መንግሥትን ያማክራል፤

፲፰/ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመቀናጀት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሬጉላቶሪ ጉዳዮችን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ጉባዔዎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዘንድ ኢትዮጵያን ይወክላል፤ የኮሙኒኬሽን አገልግሎትን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር ይከታተላል፤ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ ከአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሠራል፤

፲፱/ በቴሌኮሙኒኬሽን መስክ የሚሰጥ የቴክኒክ ትምህርት እንዲስፋፋ ከትምህርት ተቋማት ጋር ይተባበራል፤

፳/ በአዋጁ ድንጋጌዎችና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት የፈቃድ ክፍያዎችን፣ ከኦፕሬተር የሚሰበሰቡ ክፍያዎችን እና ሌሎች የሬጉላቶሪ ክፍያዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

፳፩/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍን በተመለከተ ኢትዮጵያ የተቀበለችውን ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

13/ Regulate interconnection between Telecommunications Networks of different service providers;

14/ To safeguard the interest of consumers of communications services;

15/ Investigate complaints and resolve disputes between Communications Service operators, and between consumers and Communications Service operators;

16/ Promote research into the development and use of new communications techniques and technologies, including those that promote accessibility of persons with disability and other members of society to Communications Services;

17/ Advise the government on communications policy and legislative issues in respect of providing and operating Communications Services.

18/ Represent Ethiopia, in coordination with the competent government body, in international conferences and international organizations concerned with regulation of communications services; and to monitor the implementation of treaties dealing with Communications Services to which Ethiopia is a party and to coordinate with regional and global organizations particularly with regard to use of the Radio Frequency Spectrum;

19/ Collaborate with educational institutions in order to promote technical education in the field of telecommunications;

20/ Determine and collect license fees, levies from operators and other regulatory fees consistent with the terms of this Proclamation and of other relevant laws;

21/ Ensure compliance by Telecommunications Operators with international obligations entered into by Ethiopia in the Telecommunications sector;

https://chilot.me



፳፪/ የአዋጁ ድንጋጌዎች፣ የፈቃድ ሁኔታዎች እና በአዋጁ መሠረት በባለሥልጣኑ የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ይከታተላል፣ ይመረምራል፣ ተፈጻሚነቱን ለማስከበር አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

፳፫/ የዚህን አዋጅ አፈፃፀም በሚመለከት በብሮድካስተሮች ላይ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች እና አለመግባባቶች ምላሽ ይሰጣል፣ ይፈታል፤

፳፬/ የዩኒቨርሳል አክሰስ የፋይናንስ ድጋፍ ማቋቋም እና ማስተዳደርን ጨምሮ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብን ይወስናል፣

፳፭/ የኢንፎርሜሽን ደህንነት፣ የመረጃ ግላዊነት እና ጥበቃን ያበረታታል፤

፳፮/ የኤሌክትሮኒክ ንግድ አስተማማኝ እንዲሆን የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ጥቅም ላይ በማዋል በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚደረግ ግንኙነት እውነተኛነት እና አስተማማኝነት ያረጋግጣል ፤

፳፯/ የንብረት ባለቤት ለመሆን፣ ውል ለመዋዋል እና በስሙ ለመክሰስ እና ለመከሰስ ይችላል፤

፳፰/ ዓላማውን ለማሳካትና አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## ፯. <u>የባለሥልጣኑ አደረጃጀት</u>

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ የሥራ አመራር ቦርድ፤

፪/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

## ፰. <u>የሥራ አመራር ቦርድ አባላት</u>

፩/ ባለሥልጣኑ ሰባት አባላት ባሉት የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" ተብሎ የሚጠራ) ይመራል፡፡

፪/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርድ አባላትን ይሾማል፤ ከቦርዱ አባላት መካከል አንዱን የቦርድ ሊቀመንበር ሆኖ እንዲያገለግል ይመድባል፡፡

22/ Monitor and Investigate compliance with this Proclamation and with conditions of licenses, and any Directives that the Authority may prescribe pursuant to this Proclamation and make such decisions as are necessary to enforce compliance with the same;

23/ Respond and Solve complaints and disputes against Broadcasters consistent with the ~~terms~~ implementation of this Proclamation;

24/ Determine the goal of Universal Access, including, by establishing and administering mechanisms for the financial support of Universal Access;

25/ Promote information security, data privacy and protection;

26/ To ensure electronic commerce through the use of electronic signatures to lend authenticity and integrity to correspondence in any electronic medium;

27/ To own property, to enter into contracts, and to sue and be sued in its own name;

28/ Perform such other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives and the implementation of the terms of this Proclamation.

## 7. <u>Organization of the Authority</u>

The Authority shall have:

1/ Board of Management;

2/ a Director General and, as may be necessary,Deputy Directors General, to be appointed by the Prime Minister; and

3/ the necessary staffs.

## 8. <u>Board of Management</u>

1/ The Authority shall be supervised by a Board of Management (hereinafter “the Board”) consisting of seven members.

2/ The Prime Minister shall appoint members of the Board and designate one of his nominees to serve as Chairman of the Board.

https://chilot.me


፫/ የቦርዱ አባላት አራቱ ከመንግሥት ተቋማት፣ ሶስቱ ከግሉ ዘርፍ እና የትምህርት ተቋማት የሚመረጡ ይሆናል፡፡

## ፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የአዋጁን እና የባለሥልጣኑን ተግባራት አፈፃፀም ይቆጣጠራል፤

፪/ የባለሥልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት እንዲሁም የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶች ይገመግማል ፣ ያፀድቃል፤

፫/ የዚህን አዋጅ አፈፃፀም የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን ይተገብራል፤

፬/ የዋና ዳይሬክተሩን ውሳኔዎች እና የሥራ እንቅስቃሴዎች ይገመግማል፤ ይቆጣጠራል፡፡

## ፲. የቦርድ አባላት የሚመረጡበት መስፈርት

፩/ አንድ ሰው፡-

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው፣

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ኗሪ የሆነ፣

ሐ) በባለሥልጣኑ የሥልጣን ወሰን ውስጥ ከሚገኝ ማንኛውም ተቋም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ የፋይናንስ ጥቅም የሌለው፣

መ) ከወንጀል ነፃ ከሆነ፤

ሠ) በማንኛውም ጊዜ በሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት ከኃላፊነት ያልተነሳ ከሆነ፣

የቦርድ አባል ሆኖ መሾም ወይም በአባልነት መቆየት ይችላል፡፡

፪/ የቦርዱ አባላት በፋይናንስ፣ በአካውንቲንግ፣ በሕግ፣በተጠቃሚዎች ጉዳይ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን ኢንጂነሪንግ፣ በብሮድካስቲንግ፣በጋዜጠኝነት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕዝብ አስተዳደር እና አግባብነት ባላቸው ተዛማጅ መስኮች ባሳዩት ብቃት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተመረጡ ሊሆኑ ይገባል፡፡

## ፲፩. የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን

፩/ የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

3/ Four of the members of the Board shall be from government institutions and three members of the Board shall be from the private sector and academia.

## 9. Powers and Duties of the Board

The Board shall have the following powers and duties:

1/ oversee the implementation of this Proclamation and the activities of the Authority;

2/ review and approve the annual work programs and budgets as well as the activity reports of the Authority;

3/ carry out tasks related to policy matters pertaining to the implementation of this Proclamation.

4/ review and supervise the decisions and actions of the Director General.

## 10. Requirement for Selection of the Members of the Board

1/ To be appointed or remain in office as a member of the Board, a person:

a) shall be a Citizen of Ethiopia;

b) is permanently resident in Ethiopia;

c) has no direct or indirect financial interest in any company subject to the jurisdiction of the Authority;

d) has no criminal recored

f) has not at any time been removed from an office of trust on account of misconduct.

2/ Members of the Board shall be selected by the Prime Minister based on their demonstrated qualifications in a relevant field such as finance, accounting, law, consumer affairs, telecommunications, engineering, broadcasting, journalism, information technology, economics, and public administration.

## 11. Term of Members of the Board

1/ Members of the Board shall serve for a term of five years.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የመጀመሪያው የቦርድ አባላት የሚያገለግሉበት የስራ ዘመን የተለያየ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

፫/ ማንኛውም የቦርድ አባል ለሁለተኛው የአምስት ዓመት የሥራ ዘመን እንደገና ሊሾም ይችላል፡፡

**፲፪. <u>የቦርድ አባላት ከአባልነት የሚነሱበት ሁኔታዎች</u>**

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድን የቦርድ አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያነሳ ይችላል፡-

ሀ) በህመም ምክንያት ተግባሩን በአግባቡ ለመወጣት ካልቻለ፣

ለ) ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋት ተከሶ ቢያንስ የአንድ ዓመት እስራት የተፈረደበት ከሆነ፣

ሐ) የዚህን አዋጅ የጥቅም ግጭት ድንጋጌዎች እያወቀ ጥሰት ከፈጸመ፣

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት አባል ሆኖ ለማገልገል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን አሟልቶ መቀጠል ካልቻለ፡፡

፪/ ማንኛውም የቦርድ አባል በሞት ወይም ኃላፊነቱን በመልቀቁ ወይም ከኃላፊነቱ እንዲነሣ በመደረጉ ምክንያት የአባላት መጓደል በሚፈጠርበት ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተተኪ የቦርድ አባል ይሾማል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚሾመው አዲስ የቦርድ አባል የሚያገለግለው የተሰናባቹ የቦርድ አባል ቀሪ የአገልግሎት ዘመን እስኪጠናቀቅ ብቻ ይሆናል፡፡

**፲፫. <u>የቦርዱ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩/ ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መሰብሰብ አለበት፡፡

፪/ ሊቀመንበሩ ለቦርዱ እና ለሕዝብ ከ ፲፬ ቀናት በማያንስ ጊዜ አስቀድሞ በማሳወቅ ስብሰባ የመጥራት ሥልጣን አለው፡፡ ሆኖም ከ ፲፬ ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አስቀድሞ በማሳወቅ ቦርዱ እንዲሰበሰብ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ሲኖሩ ቢያንስ ከሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት ስምምነት ካገኘ ሊቀመንበሩ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the terms of office of the members of the 1st term Board shall be staggered.

3/ A member of the Board may be re-appointed for a second five-year term.

**12. <u>Conditions for Removal of Members of the Board</u>**

1/ The Prime Minister may remove a member of the Board for the following reasons:

a) The member's incapacity to perform his or her duties due to illness;

b) The member's conviction by a court of competent jurisdiction of a criminal offense punishable by at least one year imprisonment;

c) The member's knowing and violate the conflict of interest provisions of this Proclamation;

d) The member's failure to continue to fulfill all of the qualifications for serving as a member as established in Article 10 (1) of this Proclamation.

2/ In the event of a vacancy on the Board due to the death, resignation, or removal of a member of the Board, the Prime Minister shall appoint a new member of the Board.

3/ A new member of the Board appointed pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall only serve to complete the remaining portion of the departed member's term.

**13. <u>Meeting Procedures of the Board</u>**

1/ The Board shall meet at least once a month.

2/ The Chairman shall have the power to schedule meetings, upon not less than fourteen days advance notice to the Board and to the public; provided, however, that in the event of exigent circumstances that require the Board to meet upon less than fourteen days advance notice the Chairman may call such a meeting of the Board with the concurrence of at least two other members of the Board.

https://chilot.me



፫/ በቦርዱ በወቅቱ በማገልገል ላይ ካሉት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል ፡፡

፬/ ሊቀመንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ሌላ አባል ሊቀመንበር ሆኖ እንዲመራ መወከል ይችላል፡፡ ሊቀመንበሩ በሞት፣ ከኃላፊነት በመልቀቅ ወይም በመነሳት በማይኖርበት ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አዲስ ሊቀመንበር እስኪሾም ድረስ የተቀሩት የቦርድ አባላት ከመካከላቸው አንድ አባል እንደ ሊቀመንበር እንዲያገለግል በአብላጫ ድምፅ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡

፭/ ቦርዱ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምፅ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ሆኖም ውሳኔ እንዲሰጥበት በቀረበ ጉዳይ ላይ የአባላት ድምፅ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

## ፲፬. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሲሆን በቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር ያከናውናል፤

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት የባለሥልጣኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን በተመለከተ የወቅቱን የገበያ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አጥንቶ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን ፕሮግራም እና በጀት በማዘጋጀት ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀት መሠረት ወጪዎችን ያወጣል፤

ሠ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰበሰቡ የንግድና ሌሎች ሚስጥራዊ መረጃዎችን ይጠብቃል፤

3/ A quorum of the Board shall consist the majority of the number of members of the Board then serving.

4/ In the absence of the Chairman, the Chairman may designate another member of the Board to act as Chairman. In the event of the death, resignation, or removal of the Chairman, the remaining members of the Board may, by majority vote, designate one of the remaining Board to act as Chairman pending an appointment of a new Chairman by the Prime Minister.

5/ The Board shall act by majority vote of the members present. In the event that members of the Board are evenly divided on a matter that is put to a vote by the Board, the Chairman shall cast the deciding vote.

## 14. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority and, subject to the general directions of the Board, shall direct and administer the activities of the Authority in accordance with the terms of this Proclamation.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1), the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Authority specified under Article 6 of this Proclamation;

b recruit and supervise the employees of the Authority; assess the salary and other benefits pertinent to the prevailing market conditions and submit to the government, and implement upon approval;

c) prepare and submit the work programs and budget of the Authority to the government and implement same upon approval ;

d) effect expenditures in accordance with the budget approved for the Authority;

e) safeguard commercial secrets and other confidential information collected by it pursuant to this Proclamation;

https://chilot.me



ረ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ሰ) የባለሥልጣኑን የስራ እንቅስቃሴዎች እና የፋይናንስ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ያቀርባል፡፡

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራው ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፲፭. የምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ከዋና ዳይሬክተሩ በሚሰጥ መመሪያ መሠረት፦

ሀ) የባለሥልጣኑን ተግባራት በማቀድ፣ በማደራጀት በመምራትና በማስተባበር ዋና ዳይሬክተሩን ያግዛሉ፤

ለ) የዘርፋቸውን ዕቅድ በማዘጋጀትና በማፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፤

ሐ) በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጣቸውን ሌሎች ሥራዎች ያከናውናሉ፡፡

፪/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ተለይቶ ውክልና የተሰጠው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ለዋና ዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፮. የሚኒስቴሩ ተግባር**

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት የኮሙኒኬሽን ዘርፍ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ዕድገት የሚኖረውን ጠቀሜታ ለማረጋገጥ አጠቃላይ የዘርፍ ፖሊሲ የማዘጋጀት ተግባርና ኃላፊነት አለው፡፡

**፲፯. በጀት**

፩/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

ሀ) በመንግሥት ከሚመደብ በጀት፤

ለ) በዚሁ አዋጅ አንቀጽ ፮ (፳) መሠረት ከሚሰበሰቡ የፈቃድና ሌሎች ክፍያዎች ፤

f) represent the Authority in all of its dealings with third parties; and

g) prepare the performance and the financial reports of the Authority and submit same to the concerned organ of the government;

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Authority to the extent necessary for the efficient performance of the Authority's activities.

**15. Powers and Duties of the Deputy Directors General**

1/ Deputy Directors General, subject to directions given from the Director General shall;

a) assist the Director General in planning, organizing, directing and coordinating the activities of the Authority;

b) prepare and, upon approval, implement plans of their respective departments; and

c) perform other activities assigned to them by the Director General.

2/ The Deputy Director General who is specifically delegated shall act on behalf of the Director General in his absence.

**16. Functions of the Ministry**

The Ministry shall have responsibility and function, pursuant to this Proclamation, for formulating the general policy for the Communications Sector with a view to ensuring, amongst others, the utilization of the sector as a platform for the economic and social development in Ethiopia.

**17. Budget**

1/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the budget of the Authority shall be drawn from the following sources:

a) budget allocated to it by the government;

b) income from license fees and other fees collected in accordance with Article 6(20) of this Proclamation; and

https://chilot.me



ሐ) ሌሎች ምንጮች፡፡

፪/ የባለሥልጣኑ የፋይናንስ አስተዳደር የሚመራው በፌደራል የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፰/፪ሺ፩(እንደተሻሻለ) እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው በጀት በባለሥልጣኑ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ሆኖ የባለሥልጣኑን ሥራዎች ለማስፈፀም ወጪ ይሆናል፡፡

**፲፰. የሂሳብ መዛግብት**

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ሌሎች የፋይናንስ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም የፌደራል ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

## ክፍል ሶስት
## የፈቃድ መስፈርትና ሁኔታዎች

**፲፱. ስለ ኢንቨስትመንት**

፩/ በሌላ ሕግ የተደነገገ አዋጅ ወይም ደንብ ቢኖርም ማንኛውም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብት የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የቴሌኮሚኒኬሽን ኦፕሬተር ወይም የቴሌኮሚኒኬሽን ኔትወርክ ባለቤትነት ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ምን ያህል አዲስ ኦፕሬተሮች እንደሚገቡ፣ በምን መልኩ እና መቼ ፈቃድ እንደሚሰጥ በመንግስት ይወሰናል፡፡

**፳. የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይኖረው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት አይችልም፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የፈቃድ ጊዜውን ጨምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚወስነው የፈቃድ ሁኔታዎች መሠረት የፈቃድ ዓይነቶችን በመለየት የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

c) other sources.

2/ The financial administration of the Authority shall be governed by the Federal Financial Administration Proclamation No. 648/2009 (as amended) and Regulations and Directives issued there under.

3/ Funds supplied for the Authority’s budget as described in Sub-Article (1) of this Article shall be deposited in a bank account opened in the name of the Authority and shall be expended for the performance of the Authority’s functions.

**18. Books of Accounts**

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and other financial documents of the Authority shall be audited annually by the Federal Auditor General or by an Auditor designated by him.

## PART THREE
## REQUIREMENT AND CONDITIONS OF A LICENSE

**19. Investment**

1/ Notwithstanding the terms of any other law, telecommunications services, including ownership of a Telecommunications Operator or a Telecommunications Network, shall be open without limitation to private investors including both domestic investors and foreign investors.

2/ Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the number of new entrants, the conditions and time for issuance of the licenses shall be determined by the government.

**20. Communications Services License**

1/ No person may operate a communications service without obtaining a license from the Authority.

2/ The Authority shall issue licenses for the operation and provision of communications service by way of class or individual licenses on such terms and conditions as the Authority may from time to time determine, including the term of the license.

https://chilot.me


፫/ ባለሥልጣኑ ስለፈቃድ ማመልከቻ እና የእድሳት አሰራር ሥርዓቶችን ለማዘጋጀት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ሲዘረጋ፣ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ ሲሰጥ እና እንደ አስፈላጊነቱ የፈቃድ ሁኔታዎችን ሲያዘጋጅ የሚከተሉትን መርሆዎች በመከተል እና ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፦

ሀ) ግልፅነት፣ ፍትሐዊነት እና ያለማዳላት፤

ለ) ውጤታማ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ አጠቃቀምና አስተዳደር፤

ሐ) በብሔራዊ የቁጥር ፕላን መሠረት ቁጥር መኖሩ፤

መ) በኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ፍትሐዊ ውድድርና ኢንቨስትመንትን የማበረታታት ፍላጎት፤

ሠ) ዘመናዊ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ተደራሽ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የማቅረብ ፍላጎት፣ ችሎታ፣ ብቃት እና አቅም፤ እና

ረ) ባለሥልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ እና ብሔራዊ ጥቅምን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚወስናቸው ሌሎች መርሆዎች፡፡

## ፳፩. <u>የፈቃድ ሁኔታዎች</u>

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፭) የተገለጸውን ዓላማ ለማሳካት የፈቃድ ዘመን እርዝማኔን ጨምሮ አስፈላጊ ናቸው ያለውን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት የፈቃድ ሁኔታዎች መወሰን አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ፈቃድ የሚከተሉትን የፈቃድ ሁኔታዎች እንዲይዝ ሊደረግ ይችላል፦

ሀ) ባለፈቃዱ በመላ ሀገሪቱ አድልኦ በሌለው ዋጋ አገልግሎት ማቅረብ እንዳለበት፤

3/ The Authority shall conduct a Stakeholder Consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation to establish procedures for applications for licenses and for renewal of licenses.

4/ The Authority shall at all times be guided in the formulation of licensing procedures, issuance of communications service licenses and preparation of license conditions and terms as applicable, by the principles of and consideration for—

a) Transparency, fairness and non-discrimination;

b) Efficient use and management of radio frequencies;

c) Availability of numbers under the National Numbering Plan;

d) The need to promote fair competition and investment in the communications industry;

e) The need to provide modern, quality, affordable and readily available Communications Services in all parts of Ethiopia; and

f) Such other principles and considerations as the Authority may from time to time consider necessary and in the national interest.

## 21. <u>Conditions of a License</u>

1/ The Authority shall impose such conditions on a license to operate a Communications Service, including the length of the term of the license, as the Authority deems necessary for the achievement of the objectives stated in Article 5 of this Proclamation.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Authority may include the following conditions in a license:

a) That the licensee must provide services to the entire territory of the Nation at non-discriminatory prices;

https://chilot.me



ለ) ባለፈቃዱ ከአገልግሎት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን እና ለተሰጠው አገልግሎት ተፈፃሚ የሚሆኑ ሌሎች የውል ሁኔታዎችን በፈቃዱ ውስጥ በተገለጸው ፎርም መሠረት ማሳወቅ እንዳለበት፤

ሐ) የአገልግሎት ታሪፍ ለመወሰን የሚያገለግሉ መመዘኛዎችን፤

መ) ባለፈቃዱ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎችን ጨምሮ በፈቃዱ ውስጥ የተገለፁ የቴክኒክ ደረጃዎችን እና መስፈርቶችን ማሟላት እንዳለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ የተቀመጠውን የአሰራር ሥርዓት በመከተል ማንኛውንም የፈቃድ ሁኔታዎች በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## ክፍል አራት
## የቴክኒክ ቁጥጥር

### ፳፪. የቴክኒክ ደረጃዎች

፩/ ባለሥልጣኑ የደንበኛ መገልገያ መሣሪያዎችን ጨምሮ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎችን የሚመለከቱ የቴክኒክ ደረጃዎችን ይወስናል፡፡

፪/ ደረጃዎችን ለመወሰን የሚወጣ ማንኛውም መመሪያ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት በሚካሄድ የባለድርሻ አካላት ምክክር መዘጋጀት እና በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ እና ለሕዝብ በቂ ግንዛቤ መስጠት በሚያስችሉ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ዘዴዎች ይፋ መደረግ አለበት፡፡

### ፳፫. የመሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ

፩/ ባለሥልጣኑ ከቴሌኮሙኒኬሽን ሲስተሙ ጋር ከመገጣጠማቸው በፊት የባለሥልጣኑን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ዝርዝር በመወሰን ለሕዝብ ያስታውቃል፡፡

b) That the licensee must publish, in a format specified in the license, the charges and other terms and conditions that are applicable to the service provided;

c) Criteria for setting tariffs for the service to be provided;

d) That the licensee shall comply with such technical standards or requirements including service performance standards as may be specified in the license.

3/ The Authority may modify any conditions in a license at any time, consistent with the procedural requirements established in Articles 35-38 of this Proclamation, if it considers it in the public interest to do so.

## PART FOUR
## TECHNICAL REGULATION

### 22. Technical Standards

1/ The Authority may determine technical standards regarding radiocommunications and Telecommunications Equipment including customer premises equipment.

2/ Any Directive for the determination of a standard shall be developed through a Stakeholder Consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation and shall be published on the Authority's website and in such other manner as may be appropriate to ensure adequate notice to the public.

### 23. Approval of Equipment

1/ The Authority may, by public notice, specify any radiocommunications and Telecommunications Equipment technical efficiency that requires the Authority's approval before it may be connected to a telecommunications system.

https://chilot.me



፪/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ባላቸው አገልግሎት ሰጪዎች፣ የመሣሪያ አምራቾች ወይም አስመጪዎች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የሬድዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን በተመለከተ ፍተሻ ማካሄድ እና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ሠርተፊኬት መስጠት አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማገናዘብ አለበት፡-

ሀ) በህይወት እና በጤንነት ላይ አደጋ ያለማድረስ ሁኔታዎች፤

ለ) የመረጃ ጥበቃን ጨምሮ የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ ጥገና ሁኔታ፤

ሐ) የኤሌክትሮማግኔቲክ መጣጣም ሁኔታ፤

መ) የኤሌክትሮማግኔቲክ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ተገቢ አጠቃቀም ሁኔታዎች ፤

ሠ) በቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ እና በመሣሪያው መካከል የሚኖረው መጣጣም፤

ረ) ባለሥልጣኑ በመመሪያ የሚወስናቸው ሌሎች መመዘኛዎች፡፡

፬/ የባለሥልጣኑ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸውን የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ባለሥልጣኑ በቅድሚያ ሳይፈቅድ ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ወይም ማከፋፈል የተከለከለ ነው፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚመርጣቸው ዓለም አቀፍ እውቅና ያላቸው የፍተሻ አካላት የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው የሬዲዮኮሙኒኬሽን እና የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያዎች ማስመጣት እና መጠቀምን ለመፍቀድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ በተገለፀው መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ ይችላል፡፡

2/ The Authority shall, at the request of licensed service providers, equipment manufacturers or suppliers, conduct type approval tests and issue efficacy assurance certificates for radiocommunications and Telecommunications Equipment and facilities to be used in the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3/ The Authority shall consider the following criteria to ensure technical efficiency of radiocommunications and Telecommunications Equipment:

a) Safety to life and health;

b) Maintenance of the Telecommunications Network including conditions regarding data protection;

c) Electromagnetic compatibility;

d) Appropriate use of electromagnetic frequency spectrum;

e) Interoperability between the Telecommunications Equipment and the Telecommunications Network; and

f) Other considerations that the Authority may determine by Directives.

4/ It is prohibited to manufacture, import, or distribute Radiocommunications and Telecommunications Equipment, that requires the Authorities technical efficacy assurance, without obtaining prior approval, of the Authority.

5/ The Authority may conduct a stakeholder consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation to permit the importation and use of Radiocommunication and Telecommunications Equipment that has been approved by internationally recognized testing bodies that the Authority may designate by a Directive.

https://chilot.me



## ፳፬. <u>የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አስተዳደር</u>

፩/ ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለንግድ ፣ ለመንግሥት ፣ ለሀገር መከላከያና ለብሔራዊ ደህንነት ጥቅም ላይ የሚውሉ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ለመቆጣጠር፣ ለማቀድ፣ ለማስተዳደር እና ፈቃድ ለመስጠት ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሲያስተዳድር ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ወይም ያፀደቀቻቸውን አግባብነት ያላቸው ደረጃዎች እና የዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት መስፈርቶችን እና የሬዲዮ ደንቦች በማክበር ይሆናል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዓለም አቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ሕብረት የሬዲዮ ሬጉሌሽን እና አግባብነት ያላቸው አህጉራዊ ስምምነቶች መሠረት ብሔራዊ የፍሪኩዌንሲ ድልድል ሠንጠረዥ ማዘጋጀት እና በየወቅቱ ማሻሻል አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም አጠቃቀምን በተመለከተ በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተባብራል፣ የሀገሪቱን ጥቅም በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስጠብቃል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ፈቃድ አሰጣጥ እና አጠቃቀም መመሪያ ሲያዘጋጅ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፴፭-፴፰ መሰረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ ይችላል፡፡

## ፳፭. <u>የፍሪኩዌንሲ ምደባ</u>

፩/ ባለሥልጣኑ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ ለሬዲዮኮሙኒኬሽን እና ለሬዲዮና ቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት የሚውል ፍሪኩዌንሲ ይመድባል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የፍሪኩዌንሲ አጠቃቀምን በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያስተባብራል፤ በትክክል ጥቅም ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፡፡

፫/ በፍሪኩዌንሲ ለመጠቀም በቀረበ ማመልከቻ ላይ ለመወሰን የሀገሪቱ የወቅቱና የወደፊት ፍላጎት መገናዘብ ይኖርበታል፡፡

## 24. <u>Radio Frequency Spectrum Management</u>

1/ The Authority shall be responsible for the control, planning, administration, management, and licensing of the radio frequency spectrum in Ethiopia for both commercial and government users including the military and intelligence services.

2/ In performing radio frequency spectrum management, the Authority shall comply with applicable standards and requirements of the International Telecommunication Union and its Radio Regulations as agreed or adopted by the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

3/ The Authority shall maintain, and periodically update, the "National Table of Frequency Allocations" (NTFA), in line with the Radio Regulations of the International Telecommunication Union, and relevant regional agreements;

4/ The Authority shall, in respect of radio frequency spectrum, protect the interest of Ethiopia internationally, and shall be responsible for domestic and global coordination of the use of radio frequency spectrum.

5/ The Authority may conduct one or more Stakeholder Consultations pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation to establish Directives governing the licensing and use of the radio frequency spectrum for the provision of Communications Services.

## 25. <u>Assignment of Frequency</u>

1/ The Authority shall assign frequencies to be used for telecommunications service, radiocommunication service, and for radio and television Broadcasting.

2/ The Authority shall coordinate the use of frequencies, both locally and internationally, and monitor the proper use of same.

3/ In deciding upon an application for assignment of frequencies, the Authority shall take into consideration the present use of frequencies and projected future needs of the Country.

https://chilot.me



፬/ በተመደበ ፍሪኩዌንሲ የመጠቀም ፈቃድ በጊዜ ተወስኖ ለተለያዩ ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭/ ለፍሪኩዌንሲ ምደባ በቀረቡ ማመልከቻዎች መካከል የጋራ መነጣጠል በሚኖርበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ከማመልከቻዎቹ መካከል ለመምረጥ ተገቢ ነው ብሎ ያመነውን ዘዴ መጠቀም አለበት፡፡ ከዘዴዎቹ መካከል የጨረታ ውድድር፣ ዕጣ ወይም የንጽጽር ችሎት ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

## ፳፮. የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ክፍያ

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ በተደነገገው አሰራር መሠረት የዚህን አዋጅ ዓላማ በሚያግዝ ሁኔታ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ለመጠቀም የሚያስችል የክፍያ መመሪያ ያዘጋጃል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የክፍያ መመሪያ ሲያዘጋጅ ክፍያው ቢያንስ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፦

ሀ) የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚኖረውን ተገቢ ዋጋ የንግድ ዓላማ ካላቸው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች ለመሰብሰብ እና ባለሥልጣኑ የሬዲዮ ፍሪኩዌንሲ ስፔክትረም ሀብት ለማስተዳደር፣ ፈቃድ ለመስጠት እና ለመቆጣጠር የሚያወጣውን ወጪ ለመሸፈን መቻሉን፤

ለ) ፍትሃዊ፣ አድልኦ የሌለበት እና ግልፅ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ መሆኑን፤ እና

ሐ) በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለማልማት እና ለማስፋፋት የሚያበረታታ መሆኑን፡፡

## ፳፯. ቁጥርና አድራሻ ስለመደልደል

፩/ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ፈቃድ እና በዚህ አዋጅ ለተፈቀደው ዓላማ ካልሆነ በስተቀር የቁጥር እና አድራሻ ሀብቶችን መጠቀም አይችልም፤

4/ The Authority may assign frequencies to different persons on a time-sharing basis.

5/ In the event of mutual exclusivity between applications for assignment of frequencies, the Authority shall adopt the method that it deems appropriate for selecting among the applications. Such methods may include a form of competitive bidding, random selection, or comparative hearings, among others.

## 26. Radio Frequency Fees

1/ The Authority shall prescribe such Directives, pursuant to the procedure established in Articles 35-38 of this Proclamation, as will best further the purposes of this Proclamation to establish fees for the use of radio frequency spectrum resources for the provision of Communications Services.

2/ Such Directives as the Authority may prescribe pursuant to sub-article (1) of this Article shall, at a minimum, ensure that fees:

a) recover from commercial providers of Communications Services a measure of the economic value of the radio frequency spectrum resources for the benefit of the People of Ethiopia and shall compensate the Authority for the cost of administering licensing and regulation of radio frequency spectrum resources;

b) shall be reasonable, non-discriminatory, and produced in a transparent manner; and

c) shall encourage the development and expansion of Communications Services to all areas of the Nation.

## 27. Allocation of Numbers and Addressing Resources

1/ No person shall use numbering and addressing resources in Ethiopia except pursuant to authorization of the Authority and for the purposes permitted under this Proclamation.

https://chilot.me



፪/ ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና ለኢንፎርሜሽን አገልግሎት አቅርቦት የሚውሉ የቁጥር እና የአድራሻ ሀብቶች ማስተዳደር እና መቆጣጠር አለበት፡፡ ይህም ብሔራዊ የቴሌኮሙኒኬሽን ቁጥር ዕቅድ፣ የኢንተርኔት ፕሮቶኮል አድራሻ፣ የኢንተርኔት ዶሜይን ምዝገባ እና ማንኛውም የሀገሪቱን የቁጥርና የአድራሻ ሀብት ማካተት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመከተል በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት የቁጥር ሀብት የማግኘት መብት አለው፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት አቅርቦት ቁጥር የሚያገኝበትን የአሰራር ሥርዓት ይወስናል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ የቁጥርና የአድራሻ ሀብት አስተዳደር እና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ መመሪያው የቁጥር ሀብቶች ለመጠቀም የቀረበውን ማመልከቻ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ለማድረግ የሚያስችሉ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች ማካተት ይኖርበታል፡-

ሀ) አመልካቹ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ካልሆነ፤

ለ) የተጠየቀው የቁጥር ሀብት አጠቃቀም ከብሔራዊ ቁጥር ፕላኑ ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

ሐ) የተጠየቀው የቁጥር ሀብት አጠቃቀም ከአዋጁ ድንጋጌዎች፣ ባለሥልጣኑ ካወጣው መመሪያ ወይም ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈፃሚነት ካለው ሌላ ሕግ ጋር የማይጣጣም ከሆነ፤

መ) የተጠየቀው የቁጥር ሀብት አጠቃቀም በብሔራዊ ደህንነት ወይም የሕዝብ መረጋጋት ላይ አደጋ የሚያስከትል ከሆነ፤

ሠ) አመልካቹ የቁጥር ሀብቱን በወቅቱ ወይም ውጤታማ በሆነ መንገድ የማይጠቀም ከሆነ፡፡

2/ The Authority shall manage and regulate the use of numbering and addressing resources for the provision of telecommunications services and information services in Ethiopia. This shall include the National Telecommunication Numbering Plan, Internet Protocole Address Internet domain registration, and all other numbering and addressing resources of the Nation.

3 Any Telecommunications Operators shall be entitled to obtain numbering resources for the provision of Telecommunications Services inaccordance with Directives issued following provisions of this Proclamation.

4/ The Authority shall specify the procedures by which Telecommunications Operators may obtain access to numbering resources for the provision of telecommunications services.

5/ The Authority may conduct one or more Stakeholder Consultations pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation to establish Directives governing the administration and use of numbering and addressing resources. In particular, such Directives shall include provisions for the rejection, in whole or in part, of an application for the use of numbering resources in the event that:

a) the applicant is not a Telecommunications Operator;

b) the proposed use of numbering resources is not compatible with the National Numbering Plan;

c) the proposed use of numbering resources is inconsistent with the provisions of this Proclamation, the Authority's Directives, or any other law then in force in Ethiopia;

d) the proposed use of numbering resources may pose a risk to national security or public order;

e) the applicant would not make timely or efficient use of numbering resources.

https://chilot.me



፮/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት በፀደቀው መመሪያ የቁጥር ሀብት ለመጠቀም የቀረበውን ማመልከቻ ውድቅ በሚያደርግበት ጊዜ ማመልከቻውን ውድቅ ለማድረግ ያስቻለውን ምክንያት በመግለጽ ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

6/ In any case in which the Authority shall reject an application for use of numbering resources in accordance with Directives adopted pursuant to this Proclamation, the Authority shall issue its Decision in such matter in writing and shall explain, with particularity, the reasons for rejecting the application.

፯/ አመልካቹ ባለሥልጣኑ የመጀመሪያውን ማመልከቻ ውድቅ ያደረገበትን ማንኛውንም ሕጋዊ ወይም የቴክኒክ ጉድለቶች በማሟላት በቁጥር ሀብት ለመጠቀም የተስተካከለ ማመልከቻ ማስገባት ይችላል፡፡ ሆኖም አመልካቹ በአዋጁ መሠረት ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገበትን ውሳኔ በድጋሚ እንዲያየው መጠየቅ ወይም በውሳኔው ላይ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

7/ An applicant may submit a revised application for use of numbering resources that corrects any legal or technical deficiencies that the Authority has identified in its decision rejecting the original application. An applicant may also request review by the Authority of its decision rejecting the application or may file an appeal of the decision with the Appeals Tribunal pursuant to the provisions of this Proclamation.

፰/ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት የባለድርሻ አካል ምክክር በማካሄድ የኢንተርኔት ዶሜይን ምዝገባ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

8/ The Authority shall have the power to conduct a stakeholder consultation, pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation, to establish Directives for Internet Domain Registration.

፱/ ባለሥልጣኑ በራሱ እየተቆጣጠረ ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር የሀገሪቱን የቁጥር እና የአድራሻ ሀብት ለማስተዳደር ስምምነት ሊፈጽም ይችላል፡፡

9/ The Authority shall have the power to contract with one or more organizations for the management, subject to the Authority's supervision, of the Nation's numbering and addressing resources.

## ፳፰. <u>የቁጥር ምዝገባ፣ አጠቃቀም እና ስለማዛወር</u>

## 28. <u>Number Registration, Usage and Portability</u>

፩/ ባለፈቃዱ የቁጥር መጠቀሚያ ፈቃድ ካገኘበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሶስት ዓመት ጊዜ ድረስ ቁጥሮችን አቆይቶ መጠቀም እንዲችል ባለሥልጣኑ ሊፈቅድለት ይችላል::

1/ The Authority may permit a licensee to hold numbers for later use for a period of up to three years from the date of authorization to use numbers.

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት የቁጥር አጠቃቀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ The Authority may prescribe further Directives, pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation, concerning the usage of numbers.

፫/ ባለሥልጣኑ ሁሉንም የተመደቡ ቁጥሮች እና ለልዩ አገልግሎት የተወሰኑትን ወይም ተለይተው እንዲቀመጡ የተደረጉትን እና ቁጥር የተመደበላቸው ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ያካተተ አጠቃላይ የቁጥሮች መዝገብ መያዝ አለበት፡፡ የቁጥሮች መዝገብ በፋይል ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ሊያዝ የሚችል ሲሆን ባለስልጣኑ የቁጥር መዝገቡን ለማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል ያለምንም ክፍያ ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

3/ The Authority shall maintain a general register of numbers, which contains all numbers that have been assigned and all numbers that are limited to particular uses or are stored, and the parties to whom the numbers are allocated. The register of numbers may be in physical format or electronic format and the Authority shall make the register of numbers available to any member of the public at no charge.

https://chilot.me



፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ ደንበኞች ቁጥራቸውን ሳይቀይሩ ከአንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የሚዛወሩበት አሰራር በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ ማውጣት አለበት፡፡

**፳፱. <u>የቁጥር ክፍያ</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለማስፈጸም ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና ለኢንፎርሜሽን አገልግሎት አቅርቦት የቁጥር ሀብቶች መጠቀሚያ ክፍያ ለመወሰን መመሪያ ያወጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ባለሥልጣኑ የሚያወጣው መመሪያ ክፍያው ቢያንስ የሚከተሉትን ማሟላቱን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) የቁጥር ሀብቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም የሚኖረውን ተገቢ ዋጋ የንግድ ዓላማ ካላቸው የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የኢንፎርሜሽን አገልግሎት ሰጪዎች ለመሰብሰብ መቻሉን፣

ለ) ፍትሃዊ፣ አድልኦ የሌለበት እና ግልፅ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ መሆኑን፣ እና

ሐ) በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት እና የኢንፎርሜሽን አገልግሎት ለማልማት እና ለማስፋፋት የሚያበረታታ መሆኑን፡፡

**፴. <u>የልዩ ቁጥር አገልግሎት ዓይነቶች</u>**

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለደንበኞቻቸው ማቅረብ የሚጠበቅባቸውን የልዩ ቁጥር የአገልግሎት ዓይነት ዝርዝር ለመወሰን ይችላል፡፡ የልዩ ቁጥር አገልግሎቶች የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ) የድንገተኛ አደጋ አገልግሎቶች፣

ለ) የመረጃ እገዛ አገልግሎቶች፣

ሐ) የኦፕሬተር እገዛ አገልግሎቶች፣

4/ The Authority shall conduct a Stakeholder Consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation to prescribe Directives for the implementation of number portability between Telecommunications Operators.

**29. <u>Numbering Fees</u>**

1/ The Authority shall prescribe such Directives as will best further the purposes of this Proclamation to establish fees for the use of numbering resources for the provision of Telecommunications Services and Information Services.

2/ Such Directives as the Authority may prescribe pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall, at a minimum, ensure that fees:

a) collect from commercial providers of Telecommunications Services and Information Service a measure of the value of the numbering resources for the benefit of the People of Ethiopia;

b) shall be reasonable, non-discriminatory, and produced in a transparent manner; and

c) shall encourage the development and expansion of Telecommunications Services and Information Services to all areas of the Nation.

**30. <u>Required List of Special Number Services</u>**

1/ The Authority may, through a stakeholder consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation, determine a list of services that Telecommunications Operators shall be required to provide to their customers. Such services may include, among others:

a) emergency services;

b) directory assistance services;

c) operator assistance services;

https://chilot.me



መ) ለአካል ጉዳተኛ ደንበኞች የሚሰጡ አገልግሎቶች፤ እና

ሠ) ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ሌሎች አገልግሎቶች፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የድንገተኛ አደጋ እርዳታ አገልግሎቶች ለደንበኞቻቸው እንዲያቀርቡ በሚወስንበት ጊዜ በመላ ሀገሪቱ ለስልክ አገልግሎት የተመደበ ብሔራዊ የድንገተኛ አደጋ እርዳታ ልዩ ቁጥር እንዲጠቀሙ በማድረግ የህዝብ ደህንነትን ማሳደግ እና ለድንገተኛ አደጋ እርዳታ አገልግሎት ተደራሽነት አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶች በመላ ሀገሪቱ በፈጣን ሁኔታ እንዲዘረጉ ማበረታታት ይጠበቅበታል፡፡

## ፴፩. ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን

፩/ ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሰጣቸው ውሳኔዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮች ለመመደብ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተመደበ ኢንስፔክተር የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ ወይም ማንኛውም የሬዲዮ መገናኛ መሣሪያ ይኖራል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት በሚኖረው ሥፍራ በሥራ ሰዓት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል፡፡

፫/ ኢንስፔክተሩ ማንኛውንም የቴሌኮሙኒኬሽን መሣሪያ ለመመርመርና አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ለማየትና ቅጂው እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡

፬/ ኢንስፔክተሩ ቁጥጥር ወደሚያደርግበት ማንኛውም ስፍራ ከመግባቱ በፊት የመታወቂያ ወረቀቱን ማሳየት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ለቴሌኮሙኒኬሽን መስመር መሬት እና ሕንፃዎችን ስለ መጠቀም

## ፴፪. በመሬትና ሕንፃ ስለመጠቀም

d) services for disabled customers; and

e) any other services that the Authority shall deem necessary.

2/ In the event that the Authority shall determine that Telecommunications Operators shall be required to provide access to emergency services to their customers, the Authority shall promote public safety through the use of a specific number that shall be designated as the national emergency assistance number for telephone services throughout Ethiopia. The Authority shall also take action to encourage the prompt deployment throughout Ethiopia of the necessary infrastructure for the provision of access to emergency services.

## 31. Power to Inspect

1/ The Authority may assign inspectors to ascertain that the requirements of this Proclamation and the Authority's decisions made hereunder are complied with.

2/ An inspector assigned pursuant to Sub-Article (1) of this Article may enter and inspect, during working hours, the premises of any licensee or any place on where the Authority believes on reasonable grounds there is any radio apparatus.

3/ An inspector shall have power to inspect any telecommunications equipment and to examine and make copies of any relevant documents.

4/ An inspector shall show his or her identification card before entering to any place for inspection.

## PART FIVE

## USE OF LAND AND BUILDINGS FOR TELECOMMUNICATIONS LINES

## 32. Right of Telecommunications Operator To Use Land and Building

https://chilot.me


፩/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ወደ ማንኛውም መሬት ወይም ህንፃ ከመግባቱ ከ፲ ቀን በፊት የጽሁፍ ማስታዎቂያ ለመሬቱና ለህንፃው ባለይዞታ ወይም ባለቤት በመስጠት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይችላል፡-

ሀ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ከመሬት በላይና በታች ወይም በህንፃው ላይ ማሳለፍ፣ ማስቀመጥ ወይም መትከል፤

ለ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ለመደገፍ ማንኛውንም ምሰሶ ማቆም፤

ሐ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ለመደገፍ በመሬቱ ላይ ባለ ማንኛውም ነገር ላይ ቅስት ማያያዝ ወይም ማሰር፤

መ) የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ሊጎዳ፣ እንቅፋት ሊሆን ወይም ጣልቃ ሊገባ የሚችል ማንኛውንም ዛፍ ወይም ቅርንጫፍ መቁረጥ፡፡

፪/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በግል ይዞታ ስር በሚገኝ መሬት ወይም ህንፃ ላይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተዘረዘሩትን ተግባራት ሲያከናውን ለባለይዞታው ተገቢውን የመጠቀሚያ ክፍያ ይፈፅማል፡፡ የክፍያው መጠንም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የክፍያ መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጠው ቢኖርም ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሰረት አስቀድሞ የተዘረጋ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመርን መጠገን፣ ማሻሻል፣ መፈተሽ፣ መለወጥ ወይም ማንሳት ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰው መመሪያ በባለሥልጣኑ እስኪወጣ ድረስ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተዘረጉ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሮችን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ አግባብ ባለው ሁኔታ ለመሬት ባለይዞታው ወይም ለህንፃው ባለቤት በቅድሚያ በማሳወቅ ወደ መሬቱ ወይም ወደ ህንፃው በመግባት የቴሌኮሙኒኬሽን መስመር መጠገን፣ ማሻሻል፣ መፈተሽ፣ መለወጥ ወይም ማንሳት ይችላል፡፡

1/ Any Telecommunications Operator before ten days of entering to any land or building, upon giving written notice to the lessee or possessor of the land or owner of the building may conduct the following activities:

a) pass telecommunications lines in or upon land or over, the building and establish same;

b) put up any pole, which may be required for support of a telecommunications line;

c) fasten or attach to anything growing on that land a bracket or other support for a telecommunications line;

d) cut down any tree or branch that is likely to injure, impede or interfere with any telecommunications line;

2/ Any Telecommunications Operator when performing activities indicated under Sub-Article (1) of this Article on privately possessed land or building shall pay a usage fee. The amount of usage fee shall be determined by the directive issued by the Authority.

3/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, any Telecommunications Operator can maintain, improve, examine, alter or remove a previously installed telecommunications line according to the directive to be issued by the Authority.

4/ Pending issuance of the directive required by Sub-Article (3) of this Article by the Authority, the Telecommunications Operator, upon appropriate prior notice to the lesse or possessor of the land or owner of the building, can enter to the land or building to maintain, imrove, examine, alter or remove telecommunications line which are installed before enactment of this Proclamation.

https://chilot.me



፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጠው ቢኖርም የመሬቱ ባለይዞታ ወይም የህንፃው ባለቤት ወደ ስፍራው እንዳይገባ ከከለከለው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፮/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በዚህ አንቀፅ የተደነገገውን መብት ሲጠቀም በተቻለ መጠን በመሬቱ፣ በህንፃውና በአካባቢው ላይ አነስተኛ ወይም ዝቅተኛ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ማረጋገጥ እና ላደረሰው ጉዳት ወይም ኪሳራ ለመሬቱ ባለይዞታ ወይም ለህንፃው ባለቤት ተገቢ እና በቂ ካሳ መክፈል አለበት፡፡

፯/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በመንግስት ይዞታ ስር ባለ መሬት ወይም ህንፃ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ተግባራት ሲያከናውን ለባለይዞታው ተገቢውን የመጠቀሚያ ክፍያ ይፈፅማል፡፡ የክፍያው መጠንም ባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድርን ጨምሮ ከሚመለከታቸው የክልል መስተዳድሮች ጋር በመመካከር በሚያወጣው የክፍያ መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ እና በመሬቱ ባለይዞታ ወይም በህንፃው ባለቤት መካከል የሚነሱ ማንኛውም አለመግባባቶች በባለሥልጣኑ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ወይም በመሬቱ ባለይዞታ ወይም በህንፃው ባለቤት ቅሬታ በሚቀርብበት ጊዜ ባለሥልጣኑ ለሁለቱም ወገኖች የመሰማት ዕድል በመስጠት ተቃውሞውን መርምሮ ውሳኔውን በአስር ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

፲/ በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የባለሥልጣኑ ውሳኔ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በህግ ጉዳይ ላይ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

5/ Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, the Telecommunication Operator may submit a complaint to the Authority, if the lessee or possessor of the land or the owner of the building does not allow it to enter to the premises.

6/ A Telecommunications Operator shall ensure that as little damage as possible is caused to the land or building and to the environment by reason of the exercise of the powers conferred by this Article and shall pay fair and adequate compensation to the lessee or possessor of the land or owner of the building for any damage or loss sustained by reason thereof.

7/ Any Telecommunications Operator when performing activities indicated under Sub-Article (1) of this Article on a land or building possessed by the government shall pay appropriate usage fee. The amount of usage fee shall be determined by the directive to be issued by the Authority in consultation with concerned Regional States including Addis Ababa and Diredawa city Administrations.

8/ Any dispute arising between a Telecommunications Operator and the lessee or possessor of any land or owner of any building with respect to the provisions of this Article, shall be decided by the Authority.

9/ When a complaint is submitted by a Telecommunications Operator or the lessee or possessor of any land or owner of a building with respect to the provisions of Sub-Article (8) of this Article, the Authority shall, upon giving each party an opportunity to be heard, investigate the complaint and render its decision within ten days.

10/ Any person aggrieved by a decision of the Authority may appeal to the Appeals Tribunal on legal matters within fifteen days from the date of the decision of the Authority.

https://chilot.me



**፴፫. ኮንስትራክሽን**

፩/ ማንኛውም የኮንስትራክሽን ወይም የቁፋሮ ሥራ ወይም ቋሚነት ያለው ስትራክቸር ግንባታ በቴሌኮሙኒኬሽን መስመር አቅራቢያ ከመከናወኑ በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሩን የዘረጋውን የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የስምምነት ጥያቄ ሲቀርብለት በሠላሳ ቀናት ውስጥ ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፫/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ያላግባብ ሳይስማማ በመቅረቱ ለባለስልጣኑ አቤቱታ ሲቀርብለትና ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሥራዎች በቴሌኮሙኒኬሽን መስመሩ ላይ ጉዳት የማያደርሱ ወይም የማያውኩ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ ሥራዎቹ እንዲካሄዱ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ ማንኛውም ኮንስትራክሽን ወይም ቋሚ የሆነ ስትራክቸር ግንባታ ከቴሌኮሙኒኬሽን መስመር ቢያንስ በሁለት ሜትር መራቅ አለበት፡፡

፭/ አስቀድሞ የተዘረጋ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመርን የሚያውክ ማንኛውም ግንባታ እንዲነሳ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ቢያንስ የሠላሳ ቀናት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ባለቤቱን ወይም ባለይዞታውን ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፮/ የግንባታው ባለቤት ወይም ባለይዞታ በተሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ግንባታውን ካላነሳ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ግንባታውን የማንሳት መብት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ስድስት
## የባለሥልጣኑ አሠራሮች

**፴፬. የባለሥልጣኑ የሕዝብ ውይይት የማድረግ ሥልጣን**

፩/ ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት ካለው አካል በጽሁፍ በቀረበ ጥያቄ መሠረት በዚህ አዋጅ በተሰጠው የሥልጣን ክልል ውሰጥ በሆኑ ማንኛውም ጉዳይ ላይ የሕዝብ ውይይት ሊያካሂድ ይችላል፡፡

**33. Construction**

1/ Any construction or excavation work or permanent fixtures of any nature in the vicinity of a telecommunications line shall require the prior consent of the Telecommunications Operator.

2/ The Telecommunications Operator shall have the duty to respond within thirty days to a request submitted to it pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

3/ Where the Telecommunications Operator unduly withholds its consent, the Authority may authorize the completion of the activities referred to in Sub-Article (1) of this Article where it ascertains that such activities will not cause damage or any impediment to the telecommunications line.

4/ Any construction work or fixtures of a permanent nature shall be at least two meters away from the installation of the telecommunications line.

5/ When any construction work is hindering an existing telecommunications line, the operator may, by giving thirty days' notice, request the owner or the possessor to remove it.

6/ If the owner or possessor fails to remove the construction work the operator shall have the right to remove it.

## PART SIX
## OPERATIONS OF THE AUTHORITY

**34. The Authority's Power to Conduct Public Hearings**

1/ The Authority may initiate a public hearing on any substantive matter within its jurisdiction under this Proclamation, either on its own initiative or upon the written request of interested parties.

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚካሄደው የሕዝብ ውይይት በውይይቱ ወቅት ከሚታየው ጉዳይ ሚስጥራዊነት ባህሪ የተነሳ ለህዝብ ይፋ መሆን እንደሌለበት በባለሥልጣኑ ካልተወሰነ በስተቀር ለሁሉም ሰው ክፍት መሆን አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ሂደት የመረጃ ተደራሽነትን ከሕዝቡ የሚገድብበትን ምክንያት ማሳወቅ እና በተቻለ መጠን ሁሉም የውይይት መድረኮች ሙሉ በሙሉ ለሕዝብ ክፍት መሆናቸውን ለማረጋገጥ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡

፴፭. **የባለሥልጣኑ የባለድርሻ አካላት ምክክር ሁኔታዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ወገን መብት ወይም የሕዝብ ጥቅም ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ በሚችል በማንኛውም በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ ባለ ጉዳይ ላይ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በጽሁፍ ብቻ እንዲቀርብ በማድረግ የባለድርሻ አካላት ምክክር ማካሄድ አለበት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የባለድርሻ አካላት ምክክር ለማካሄድ ሲፈልግ እንደሚከተለው በሕዝብ ማስታዎቂያ ማሳወቅ አለበት፦

ሀ) የሂደቱን መጀመር ማሳወቅ፤

ለ) ከባለድርሻ አካላት ምክክር ጋር የሚያያዘውን ጉዳይ መለየት፤,

ሐ) የማመልከቻ መስፈርቶችን ጨምሮ አስተያየት መቅረብ የሚችልበትን ጊዜ መግለጽ፤

መ) ፍላጎት ላላቸው አካላት አስተያየት ዝግጅት የሚረዱ ማንኛውንም የውይይት መነሻ ጽሁፍ ወይም ሌሎች መረጃዎችን መስጠት፤ እና

ሠ) ባለሥልጣኑ እንደ ሁኔታው ተገቢ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎች፡፡

2/ Public hearings conducted by the Authority shall be open to all members of the public, except to the extent that the Authority decides that the confidential nature of any specific matter to be addressed during the hearing requires that such confidential material be withheld from public disclosure.

3/ The Authority shall make public the reasons for limiting public access to information in any of its proceedings and shall seek to ensure to the maximum extent possible that all of its proceedings shall be fully open to the public.

35. **The Authority's Conditions for Stakeholder Consultation**

1/ The Authority shall hold a stakeholder consultation, to be conducted in whole or in part by written submissions only, whenever it may take action in any matter within its jurisdiction that may affect the rights of any party or the public interest.

2/ The Authority shall initiate a stakeholder consultation by issuing a public notice:

a) announcing the commencement of the process;

b) setting out the nature of the matter to which such stakeholder consultation relates;

c) stating the period within which comments may be submitted, together with all filing requirements;

d) providing any background discussion paper or other information that may assist interested parties in the preparation of their comments; and

e) including any other information that the Authority deems appropriate in the circumstances.

https://chilot.me


፫/ የባለድርሻ አካላት ምክክር ለማካሄድ የሚወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ በባለሥልጣኑ እየታዩ ያሉ ጉዳዮች እና በባለድርሻ አካላት ምክክር ውጤት መሠረት ከባለሥልጣኑ የሚጠበቁ ውሳኔዎች ላይ ፍላጎት ላላቸው አካላት በቂ ግንዛቤ የሚሰጥ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ያዘጋጀውን ማንኛውም መመሪያ ከባለድርሻ አካላት ምክክር በተገኘው ውጤት መሠረት ለማፅደቅ፣ ለማሻሻል ወይም ለመሻር ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለማስፈፀም እርምጃ ባለመውሰድ ወይም በባለድርሻ አካላት ምክክር ውጤት መሠረት የደረሰበትን ግኝት ሪፖርት በማውጣት ጉዳዩን ሊቋጨው ይችላል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ ሲያምንበት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ሊታዩ የማይችሉ ጉዳዮች መፍትሄ እንዲያገኙ ሕግ እንዲወጣ ሀሳብ ማቅረብ ወይም እንደ ሁኔታው አግባብ ሌላ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

**፴፮. የባለሥልጣኑ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት**

፩/ ባለሥልጣኑ ማንኛውም የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ግልፅነት ባለው መንገድ መካሄዱን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ማንኛውንም መመሪያ ለማፅደቅ፣ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለመተግበር ሲፈልግ በሕዝብ ማስታወቂያ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴ ለሕዝብ በቂ መረጃ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ሊወስድ ስለሚያስበው ማንኛውም እርምጃ በተመለከተ የተሰጠው ሥልጣን የሚመለከታቸው አካላትን ጨምሮ ህብረተሰቡ እና ተጠቃሚዎች በጽሁፍ ወይም በቃል አስተያየት እንዲያቀርቡ በቂ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በቀረቡ የጽሁፍ ወይም የቃል አስተያየቶች ላይ ህብረተሰቡ አስተያየት እንዲሰጥ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

3/ The Authority shall ensure that the Public Notice initiating a stakeholder consultation shall give interested parties adequate notice of the matters that the Authority is considering and the actions that the Authority is likely to take as a result of the stakeholder consultation.

4/ As a result of a stakeholder consultation, the Authority may adopt, amend, or repeal any Directive that it is within its power to formulate in accordance with the provisions of this Proclamation. The Authority may also conclude that the purposes of this Proclamation will be best served by not taking action or by issuing a report concerning the findings it reaches as a result of the stakeholder consultation.

5/ When the Authority considers it appropriate, it may also present recommendations to Parliament for legislation to address matters that the Authority considers it cannot address pursuant to the terms of this Proclamation or may take such other action as it considers appropriate in the circumstances.

**36. The Authority's Decision Making Process**

1/ The Authority shall ensure that it shall conduct all of its proceedings in a transparent manner.

2/ The Authority shall provide adequate notice to the public, through a Public Notice or other similar instrument, of its proposed action with respect to adoption, amendment, repeal, or enforcement of any Directive or its proposed action to implement any provision of this Proclamation.

3/ The Authority shall allow members of the public, including the concerned bodies the consumers, and other organizations a reasonable opportunity to submit written or oral presentations addressing any action the Authority proposes to take.

4/ The Authority shall also allow members of the public to respond to written or oral presentations submitted by other members of the public.

https://chilot.me



## ፴፯. የባለሥልጣኑ ውሳኔ

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ከባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር ጋር የሚጣጣሙ ማንኛውንም እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በቀረበለት ማንኛውም ጉዳይ ላይ ምክንያቱን በመግለጽ በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፫/ የባለሥልጣኑ ውሳኔ በክርክሩ ጊዜ በቀረቡ የመከራከሪያ መረጃዎች እና ግንዛቤ በወሰደባቸው እውነታዎች ላይ ብቻ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

፬/ የባለሥልጣኑ ውሳኔ በህብረተሰቡ የቀረቡ ሀሳቦችን እና ውሳኔውን ለመስጠት ያስቻሉትን ምክንያቶች በተገቢው ሁኔታ ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

፭/ የባለሥልጣኑ ውሳኔ ማንኛውም ወገን የሚያቀርበውን ጥያቄ በሙሉ ወይም በከፊል ሊቀበለው፣ ውድቅ ሊያደርገው ወይም በተሰጠው የሥልጣን ወሰን አዋጁን በተሻለ ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል ሌላ መፍትሔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፮/ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው እያንዳንዱ ውሳኔ ላይ ህብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ውሳኔውን በራሱ ድረ-ገጽ እና ሰፊ የስርጭት ሽፋን ባላቸው ተገቢ ህትመቶች በይፋ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ፴፰. የባለሥልጣኑ ውሳኔ በድጋሚ ስለሚታይበት ሂደት

፩/ በባለሥልጣኑ ወይም በባለሥልጣኑ ሠራተኛ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ባለሥልጣኑ ወይም ሠራተኛው የሰጠው ውሳኔ በባለስልጣኑ በድጋሚ እንዲታይለት መጠየቅ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ውሳኔው በድጋሚ እንዲታይ በተጠየቀበት ሁሉም ጉዳዮች ላይ ፍላጎት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በጽሁፍም ሆነ በቃል ሃሳባቸውን እንዲገልፁ ዕድል ለመስጠት ውሳኔው በድጋሚ በመታየት ላይ መሆኑን በይፋ ለህዝብ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 37. The Authority's Decisions

1/ The Authority may take any action that is consistent with the Authority's powers and duties pursuant to this Proclamation.

2/ In any proceeding before the Authority, the Authority shall render a decision in writing explaining the reasons for its action.

3/ The Authority shall base its findings of fact and conclusions of law only upon the information contained in the record of the proceeding before it and on publicly available facts of which the Authority may take official notice.

4/ The Authority's decision shall explain in reasonable detail the reasons supporting its action and shall address the opinion presented by members of the public.

5/ The Authority's decision may grant or deny in whole or in part, any action or relief requested by any party; or may fashion such other remedy within the scope of the Authority's power that may, in the Authority's judgment, best serve the purposes of this Proclamation.

6/ The Authority shall publish each decision on the Authority's website and in appropriate publications having wide circulation in order to ensure that the public has adequate notice of its Decision.

## 38. The Authority's Decision Review Process

1/ Any person aggrieved by the decisions of the Authority or the Authority's staff may request that the Authority review the decision of the Authority or of the Authority's staff.

2/ In all cases in which such review is requested, the Authority shall issue a Public Notice informing the public that the decision is under review and shall allow interested members of the public an opportunity to make written or oral presentations concerning the request for review of the decision.

https://chilot.me



፫/ ባለሥልጣኑ ውሳኔው በድጋሚ እንዲታይ የቀረበለትን ጥያቄ በከፊል ወይም በሙሉ ሊቀበለው ወይም ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፣

፬/ ባለሥልጣኑ ውሳኔውን በድጋሚ እንዲያይ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ ውሳኔውን ለመስጠት ያስቻለውን ምክንያት በመግለፅ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

**፴፱. <u>የይግባኝ ሰሚ አካል</u>**

፩/ ሶስት አባላት ያሉት የይግባኝ ሰሚ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት ለሶስት ዓመት የሥራ ዘመን እንዲያገለግሉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሾማሉ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የመጀመሪያው የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት የሚያገለግሉበት የስራ ዘመን የተለያየ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

፬/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከይግባኝ ሰሚ አካል አባላት መካከል አንዱን የይግባኝ ሰሚ አካል ሊቀመንበር ሆኖ እንዲያገለግል ይሾማል፡፡

፭/ የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት ለሁለተኛው የሶስት ዓመት የሥራ ዘመን እንደገና ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

፮/ የይግባኝ ሰሚ አካል አባላት በሕግ፣ በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በብሮድካስቲንግ ወይም ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ዘርፎች ልምድ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡

፯/ የይግባኝ ሰሚ አካል ከባለሥልጣኑ ክፍያ ማግኘት አለባቸው፡፡ ነገር ግን ክፍያው በሥራ ዘመናቸው ሊቀነስ አይችልም፡፡

**፵. <u>የይግባኝ ሰሚ አካል ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ የይግባኝ ሰሚ አካል በባለሥልጣኑ የተሰጡ ውሳኔዎችን በይግባኝ ለመስማት ሥልጣን አለው፡፡

፪/ የይግባኝ ሰሚ አካል የሚቀርቡለትን ጉዳዮች የሚሰማበትና ውሳኔ የሚሰጥበትን የአሰራር ሥርዓት ማዘጋጀት አለበት፡፡

3/ The Authority may grant or deny the request for review in part or in whole

4/ The Authority shall issue a written decision in response to the request for review of the original decision and shall state with particularity the reasons underlying its action.

**39. <u>Appeals Tribunal</u>**

1/ An Appeals Tribunal with a three memebers is hereby established by this proclamation.

2/ The Appeals Tribunal members shall to be appointed by the Prime Minister and serve for three years.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (2) of this Article, the terms of office of the members of the Appeals Tribunal shall be staggered.

4/ The Prime Minister shall designate one of his nominees to serve as Chairman of the Appeals Tribunal.

5/ Members of the Appeals Tribunal may be reappointed for a second three-year term.

6/ Members of the Appeals Tribunal shall have experience in law, telecommunications, broadcasting or other relevant disciplines.

7/ Members of the Appeals Tribunal shall be remunerated by the Authority, but the remuneration of a member of the Appeals Tribunal may not be decreased during his term of office.

**40. <u>Powers and Duties of Appeals Tribunal</u>**

1/ The Appeals Tribunal shall be empowered to hear appeals of decisions taken by the Authority.

2/ The members of the Appeals Tribunal shall establish transparent procedures for hearing and adjudicating matters brought before them.

https://chilot.me



፫/ በባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም አካል በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ ለይግባኝ ሰሚ አካል ይግባኝ ሊል ይችላል፡፡

፬/ ማንኛውም በባለሥልጣኑ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ የይግባኝ ጥያቄ ውሳኔው ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ በሠላሳ ቀን ውስጥ ለይግባኝ ሰሚ አካል መቅረብ አለበት፡፡

፭/ የይግባኝ ሰሚ አካል የባለሥልጣኑን ውሳኔ ያፀናበት፣ የሻረበትን ወይም እንደገና እንዲታይ ያዘዘበትን ምክንያት በማብራራት ውሳኔውን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፮/ የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች በተመለከተ ባለሥልጣኑ ውሳኔው የሚፀናበትን የተለየ ቀን በጽሁፍ ካላሳወቀ በስተቀር ውሳኔው ለሕዝብ ይፋ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

፯/ የውሳኔውን ተፈፃሚነት ማዘግየት የፍትህና የአዋጁን ዓላማ በተሻለ ሁኔታ ለመተግበር የሚጠቅም ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የባለሥልጣኑ ውሳኔ በድጋሚ እንዲታይ ቢጠየቅም ወይም ይግባኝ ቢቀርብበትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፰/ በይግባኝ ሰሚ አካል ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስልሳ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ ጉዳይ ላይ ብቻ ይግባኝ ማለት ይችላል፡፡ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ፵፩. ስለ የባለሥልጣኑ የጥቅም ግጭት መርህ

፩/ ከባለሥልጣኑ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ዋና ዳይሬክተሩም ሆነ የሥራ አመራር ቦርድ አባል፣ የይግባኝ ሰሚ አካል አባል ወይም ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሰራተኛ በራሱ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ በሚችሉ በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ መስራት አይችልም፦

ሀ) የራሱን የግል የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

ለ) የባለቤቱን ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጁን የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

ሐ) የራሱን የንግድ አጋር የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤

3/ Any person aggrieved by a decision of the Authority may appeal to Appeals Tribunal only for legal matters.

4/ Any request for appeal of the decision by the Authority must be filed with the Appeals Tribunal within thirty days of the effective date of the decision by the Authority.

5/ The Appeals Tribunal shall issue its decisions in writing, explaining its reasons for affirming, overruling or ordering review of the decisions of the Authority.

6/ For purposes of this subsection, a decision of the Authority shall be effective upon its public release unless the Authority shall specify a different effective date in writing.

7/ A Decision of the Authority shall be effective during the pendency of any request for review or appeal, unless the interests of justice and the purposes of this Proclamation shall be better served by delaying the effectiveness of such Decision.

8/ Any person aggrieved by a decision of the Appeals Tribunal may within sixty days from the date of the decision appeal to the Federal High Court, only for error of law. The decision rendered by the Federal High Court shall be final.

## 41. The Authority's Conflict of Interest Code

1/ Neither the Director General nor any member of the Board, the Appeals Tribunal member, nor any member of the Authority's staff may work on any Authority matter that will affect:

a) his or her personal financial interests;

b) the financial interests of his or her spouse or minor child;

c) the financial interests of his or her business partner;

https://chilot.me


መ) በኦፊሰርነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በአጋርነት፣ በሰራተኝነት ወይም በባለአደራነት የሚያገለግለውን የማንኛውም ተቋም የፋይናንስ ጥቅም በሚመለከት፤ ወይም

ሠ) በሥራ ለተቀጠረበት ወይም ለሥራ ቅጥር በድርድር ላይ የሚገኝበትን የማንኛውም አካል የፋይናንስ ጥቅም ጋር በሚገናኝ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለጹት ሁኔታዎች ሲኖሩ ማንኛውም የባለሥልጣኑ አካል ለጥቅም ግጭት ምክንያት የሆነውን ነገር መተው ወይም በጉዳዩ ውስጥ ላለመሳተፍ እራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡

፫/ በማናቸውም ሁኔታ እንኳን ቢሆን ዋና ዳይሬክተሩ፣ ማንኛውም የሥራ አመራር ቦርድ አባል፣ ማንኛውም የይግባኝ ሰሚ አካል አባል ወይም ማንኛውም የባለሥልጣኑ ሠራተኛ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቆጣጠረው ማንኛውም ኩባንያ ቀጥተኛ የባለቤትነት ጥቅም ሊኖረው አይችልም፡፡

## ክፍል ሰባት
## ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር

### ፵፪. ስለ ኢንተርኮኔክሽን

አንድ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ከሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኢንተርኮኔክሽን ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፵፫) በተመለከቱት መርሆዎች እና ሁለቱ ወገኖች በድርድር በሚስማሙበት የውል ሁኔታዎች መሠረት የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርኩን ከሌላኛው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ኔትወርክ ጋር ቴክኒካዊ አግባብነት ባለው ቦታ ኢንተርኮኔክት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

### ፵፫. የኢንተርኮኔክሽን የስምምነት ሁኔታዎች

፩/ በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ማንኛውም የኢንተርኮኔክሽን ስምምነት በዚህ አዋጅ እና በአዋጁ መሰረት ባለሥልጣኑ በየጊዜው ከሚያወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ እና በጽሁፍ መሆን አለበት፡፡

d) the financial interests of any organization in which he or she serves as an officer, director, general partner, employee or trustee; or

e) the financial interests of any entity with whom he or she has an arrangement for employment or with whom he or she is negotiating for employment.

2/ In such case, he or she may either divest himself of the interest causing the conflict of interest or recuse himself from any involvement in the matter.

3/ In no instance, however, may the Director General, any member of the Board, any member of the Appeals Tribunal, nor any member of the Authority's staff hold a direct ownership interest in any company that is subject to the jurisdiction of the Authority pursuant to this Proclamation.

## PART SEVEN
## ECONOMIC REGULATION

### 42. Interconnection

If a Telecommunications Operator receives a request for interconnection from another Telecommunications Operator, shall have an obligation to interconnect its Telecommunications Network with the other Telecommunications Operator's Telecommunications Network at technically feasible locations, in accordance with the principles specified in Article (43) of this Proclamation and pursuant to terms and conditions negotiated between the parties.

### 43. Terms and Conditions for Interconnection

1/ All interconnection agreements between Telecommunications Operators shall be in writing and shall comply with this Proclamation, and the Directives published from time to time by the Authority pursuant to this Proclamation.

https://chilot.me



፪/ የኢንተርኮኔክሽን የውል ስምምነት ሁኔታዎች በዋናነት በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረስበት ስምምነት ይወሰናል፡፡ ሆኖም የሚከተሉት ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በራሱ ወይም በአንዱ ወይም በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ሲጠየቅ ጣልቃ በመግባት ተፈፃሚነት ያለው ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፦

ሀ) ስምምነቱ ወይም የስምምነቱ የውል ሁኔታዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ባለስልጣኑ ካፀደቃቸው ማናቸውም መመሪያዎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ለ) ሁለቱ ወገኖች በተወሰኑ ጉዳዮች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ወይም ስምምነት ላይ ለመድረስ መዘግየት ሲኖር፤ ወይም

ሐ) የሕዝብን ጥቅም ከግምት በማስገባት በአንዱ ወይም በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ጥያቄ ባይቀርብለትም የባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ጣልቃ መግባት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፡፡

## ፵፬. ኮሎኬሽን እና መሰረተ ልማት መጋራት

፩/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሕዝብ አገልግሎት ለመስጠት ዓላማ ባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ብሎ ከለየው ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ስፍራ ላይ መሣሪያዎቹ በኮሎኬሽን እንዲቀመጡለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ በኮሎኬሽን መሣሪያዎችን እንዲያስቀምጥ የተጠየቀው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ቴክኒካዊ አግባብነት እስካለው ድረስ ጥያቄውን መቀበል አለበት፡፡

፫/ የኮሎኬሽን ቦታ አጠቃቀም በተመለከተ የሚኖረውን ክፍያ ሁለቱ ወገኖች በድርድር መስማማት አለባቸው፡፡

፬/ በኮሎኬሽን ስምምነት የንግድ ወይም የቴክኒክ ሁኔታዎች ላይ ሁለቱ ወገኖች ካልተስማሙ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ ፴፭-፴፰ በተገለፀው መሠረት ተገቢ የስምምነት ሁኔታዎች ላይ መወሰን አለበት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ የቴክኒክ ደረጃ እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የኮሎኬሽን ቦታን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

2/ The terms and conditions of interconnection agreements shall primarily be agreed upon between the parties thereto; however, the Authority may intervene and make binding rulings at its own instance or with request of either or both parties to the agreement:

a) if the agreement or any provision thereof is inconsistent with the provisions of this Proclamation or any Directive that the Authority has adopted;

b) in the event of a failure of consensus between the parties on specific issues or a delay in reaching such consensus; or

c) if the Authority considers it is in the public interest for it to intervene at its own instance and without any invitation from either or both parties to the agreement.

## 44. Collocation and Infrastructure Sharing

1/ A Telecommunications Operator may request physical collocation of its equipment, for the purposes of providing a service to the public, at the premises of another Telecommunications Operator that the Authority has determined has significant market power.

2/ The Telecommunications Operator that receives a request for physical collocation shall accommodate such request to the extent it is technically feasible.

3/ The parties shall, negotiate reasonable compensation for the use of collocation space.

4/ In the event that the parties cannot agree on commercial or technical terms of a collocation agreement, the Authority shall determine the appropriate terms pursuant to the procedure established in Articles 35-38 of this Proclamation.

5/ The Authority shall have power to prescribe Directives for the provision of collocation space, including standard technical and commercial terms.

https://chilot.me



፮/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ለመሥጠት ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ-ልማቶችን በተቻለ መጠን እንዲጋሩ ይበረታታሉ፡፡

፯/ በባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የታመነበት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ያለውን ቋሚ እና ገባሪ መሠረተ-ልማት ተገቢ ጥያቄ ላቀረበ ሌላ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ማጋራት አለበት፡፡

፰/ መሰረተልማት መጋራትን በተመለከተ የሚኖረውን ክፍያ ሁለቱ ወገኖች በድርድር መስማማት አለባቸው፡፡

፱/ በመሰረተልማት መጋራት ስምምነት የንግድ ወይም የቴክኒክ ሁኔታዎች ላይ ሁለቱ ወገኖች ካልተስማሙ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ በተገለፀው መሠረት ተገቢ የስምምነት ሁኔታዎች ላይ መወሰን አለበት፡፡

፲/ ባለሥልጣኑ የቴክኒክ ደረጃ እና የንግድ ሁኔታዎችን ጨምሮ የመሰረተልማት መጋራትን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

፲፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፲) የተደነገገው ቢኖርም በባለሥልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ ያለው ስለመሆኑ ባይወሰንም ለማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የኮሎኬሽን ወይም የመሰረተልማት መጋራት ጥያቄ ለማቅረብ የሚከለክል ሁኔታ የለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ በሚኖርበት ጊዜ ሁለቱ ወገኖች በኮሎኬሽን ወይም የመሠረተልማት መጋራት የንግድ እና የቴክኒክ ሁኔታዎች ላይ መደራደር አለባቸው፡፡

## ፵፭. ሕጋዊ ታሪፍ

፩/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ለሚሰጠው አገልግሎት ሕጋዊ ክፍያ ማስከፈል አለበት፡፡ ሕጋዊ ተመኑ ፍትሀዊ፣ ተገቢ እና በተጠቃሚዎች መካከል አድልኦ የማያደርግ መሆን አለበት፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ ወይም ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንደሌላቸው የተለዩ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍ ሕጋዊ እንደሆነ ይገመታል፣ ታሪፋቸውንም ለባለስልጣኑ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም፡፡

6/ Telecommunications Operators are encouraged, to the maximum extent feasible, to share passive and active infrastructure for the provision of telecommunication service.

7/ A Telecommunications Operator that the Authority has determined has significant market power shall be required to share both passive and active infrastructure upon the reasonable request of another Telecommunications Operator.

8/ The parties shall, negotiate reasonable compensation for the sharing of infrastructure.

9/ In the event that the parties cannot agree on commercial or technical terms of an agreement for the sharing of infrastructure, the Authority shall determine the appropriate terms pursuant to the procedure established in Articles 35-38 of this Proclamation.

10/ The Authority shall have power to prescribe Directives for the sharing of infrastructure, including standard technical and commercial terms.

11/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1)-(10) of this Article, nothing in this Proclamation shall be deemed to prevent a Telecommunications Operator from requesting collocation or infrastructure sharing of a Telecommunications Operator that the Authority has not determined to have significant market power. In the event that such a request is made, the parties shall seek to negotiate the commercial and technical terms of such collocation or infrastructure sharing.

## 45. Lawful Tariffs

1/ All Telecommunications Operators shall charge lawful tariffs for their services. Lawful rates shall be just, reasonable, and not unduly discriminatory among users or classes of users.

2/ All tariffs of Telecommunications Operators that have not been found by the Authority to possess significant market power, as defined in this Proclamation or by the Authority's Directive, shall be presumed lawful; and shall not be required to file their tariffs with the Authority.

https://chilot.me



፫/ ማንኛውም በባለሥልጣኑ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ የአገልግሎት ገበያ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የታመነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የአገልግሎት ታሪፉን በግልፅ ማሳወቅ አለበት፡፡

፬/ በባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው የታመነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ያወጣው ታሪፍ በባለሥልጣኑ እስኪፀድቅ ድረስ ተፈፃሚነቱ እንዲዘገይ ባለሥልጣኑ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ በተደነገገው መሠረት በሚያፀድቀው መመሪያ በባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በታመነ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር የቀረበውን ታሪፍ ሕጋዊነት የሚወስንበትን ደረጃ እና የአሰራር ሥርዓት ያዘጋጃል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የሚዘጋጀው ደረጃ እና የአሰራር ሥርዓት ወጪን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ ወጪን ሲገመግም ወደፊት ሊኖር የሚችለውን የወጪ ጭማሪ የዋጋ ዘዴ መጠቀም አለበት፡፡

## ፵፮. የባለሥልጣኑ ታሪፍ የመገምገም ሥልጣን

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ የማንኛውም ፈቃድ ያለው የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ለመገምገም፣ ለመቆጣጠር እና ታሪፉ ሕጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የታሪፍ ዝግጅት መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በማንኛውም ፍላጎት ያለው አካል ለቀረበ ማመልከቻ ምላሽ ለመስጠት የማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፐሬተር ታሪፍ ሕጋዊ መሆኑን ማጣራት ይችላል፡፡ ባለሥልጣኑ እንዲህ ዓይነት ማጣራት በሚያደርግበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ በተደነገገው መሰረት የሚያዘጋጃቸውን መስፈርቶች በመጠቀም ይሆናል፡፡

## ፵፯. የገበያ ውድድር ቁጥጥር

በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም ባለሥልጣኑ በአጠቃላይ ወይም በተለየ ሁኔታ የኢትዮጵያን የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገበያ በተመለከተ ለመወሰን፣ ለማስተዳደር፣ ለመቆጣጠር እና

3/ Any Telecommunications Operator that the Authority determines possess significant market power, in one or more relevant product markets shall publish its tariffs.

4/ The Authority may direct that a Telecommunications Operator that the Authority has determined possesses Significant Market Power delay the effectiveness of any tariff until the Authority has approved said tariff.

5/ The Authority may, by Directive adopted pursuant to the procedure established in Articles 35-38 of this Proclamation, establish the standards and procedures by which it shall determine the lawfulness of any tariff filed by a Telecommunications Operator that the Authority has determined possesses significant market power.

6/ Such standards established under Sub-Article (5) of this Article shall, *inter alia*, include the cost basis on which the tariff was established. In assessing cost, the Authority shall use a forward-looking incremental cost methodology.

## 46. The Authority's Power To Review Tariffs

1/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the Authority shall have the power to review and control tariffs of any licensed Telecommunications Operator and to develop Directives for setting tariffs in order to ensure that such tariffs are lawful.

2/ The Authority may, on its own motion, or in response to a petition filed by any interested party, initiate a proceeding to observe whether the tariffs of any Telecommunications Operator are lawful. In making such observation the Authority may rely on standards that it may develop pursuant to the Provisions established in Articles 35-38 of this Proclamation.

## 47. Market Competition Regulation

Notwithstanding the provisions of any other law, the Authority shall have exclusive power to determine, pronounce upon, administer, monitor and enforce compliance of all persons with

https://chilot.me



ማንኛውም ሰው ለውድድር ሕግና መመሪያ ተገዢ እንዲሆን ለማስፈፀም ብቸኛ ሥልጣን አለው፡፡

## ፵፰. የገበያ ውድድርን ስለመከላከል

፩/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በየትኛውም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ማንኛውም ተግባር ላይ ተሳትፎ ከተገኘ ሕገ-ወጥ ድርጊት እንደፈፀመ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

፪/ ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በየትኛውም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ያለው ተግባር ለመፈፀም በማቀድ ካለ ሰው ጋር ስምምነት ከፈፀመ ሕገ-ወጥ ድርጊት እንደፈፀመ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት ወይም በማንኛውም ፍላጎት ያለው አካል ለቀረበ ማመልከቻ ምላሽ ለመስጠት የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች በየትኛውም የኢትዮጵያ የቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ማንኛውም ድርጊት ላይ መሳተፋቸውን ማጣራት ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ በተቀመጡት የአሰራር ሥርዓት መሠረት ማንኛውም የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር በየትኛውም የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ገበያ ውስጥ ውድድርን በእጅጉ የመቀነስ ዓላማ ወይም ውጤት ባለው ማንኛውም ድርጊት ላይ መሳተፉን ባረጋገጠበት ጊዜ፦

ሀ) ለወደፊቱ ከእንዲህ ዓይነት ተግባር እንዲቆጠብ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ወይም አገልግሎት ሰጪው ትዕዛዝ ይሰጣል፤ እንዲሁም

ለ) እንደሁኔታው አግባብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ (፶፪) በተደነገገው መሠረት ቅጣት ወይም ሌላ እገዳ ይጥልበታል፡፡

## ፵፱. የዩኒቨርሳል አክሰስ አገልግሎት

፩/ ባለሥልጣኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚደረግ ምክክር መሰረት ለሀገሪቱ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ዓመታዊ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብ ማዘጋጀት አለበት፡፡

competition laws and Directives, whether of a general or specific nature, as it relates to the Ethiopian Communications Service market.

## 48. Regulation of Anti-competitve Practices

1/ It shall be unlawful for any Telecommunications Operator to engage in any conduct that has the purpose or effect of substantially lessening competition in any Ethiopian telecommunications market.

2/ It shall be unlawful for any Telecommunications Operator to enter into an agreement or arrangement with any other person that has the purpose or effect of substantially lessening competition in any Ethiopian telecommunications market.

3/ The Authority may, on its own motion, or in response to a petition filed by any interested party, initiate a proceeding to observe whether or not Telecommunications Operators has engaged in any conduct that has the purpose or effect of substantially lessening competition in any Ethiopian telecommunications market.

4/ In accordance with the procedures established in Articles 35-38 of this Proclamation, in the event that the Authority finds that any Telecommunications Operator has engaged in any conduct that has the purpose or effect of substantially lessening competition in any Ethiopian telecommunications market the Authority shall:

a) order such Telecommunications Operator or service provider to refrain from such conduct in the future; and

b) impose such fine or other suspension as prescribed pursuant to Article 52 of this Proclamation, as it deems appropriate in the circumstances.

## 49. Universal Access Services

1/ The Authority shall, pursuant to Stakeholder Consultation, develop annual objectives for Universal Access to Communications Services in Ethiopia.

https://chilot.me



፪/ ባለሥልጣኑ የዩኒቨርሳል አክሰስ ግብ በሚያዘጋጅበት ጊዜ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች በተለይ በገጠር እና ርቀት ባላቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች በተቻለ መጠን ከፍተኛ ቁጥር ላላቸው ተጠቃሚዎች ተደራሽ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ ለኮሙኒኬሽን አገልግሎት ዩኒቨርሳል አክሰስ ድጋፍ የሚውል የዩኒቨርሳል አክሰስ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡ የፈንዱ የገቢ መጠንና ምንጭ እንዲሁም ፈንዱ ስለሚተዳደርበት ሁኔታ በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፶. <u>የተጠቃሚዎች መብት ጥበቃ</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች መብት የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚያወጣውን መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሰረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ ማፅደቅ አለበት፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተሰጠው ሥልጣን ሳይገደብ እያንዳንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ተጠቃሚዎች ለቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ ወይም ለባለሥልጣኑ ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉበትን ሥርዓት ጨምሮ የተጠቃሚዎችን መብት የሚደነግግ የሥነ-ምግባር ኮድ እንዲያዘጋጅ መጠየቅ ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ መሠረት የባለድርሻ አካላት ምክክር በማካሄድ እያንዳንዱ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ያዘጋጀውን የሥነ-ምግባር ኮድ በጽሁፍ ውሳኔ ማፅደቅ አለበት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በባለድርሻ አካላት ምክክር የተለዩ ጉዳዮች የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆነው ሲገኙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሩ የሥነ-ምግባር ኮዱን በዚሁ መሠረት እንዲያሻሽል መጠየቅ ይችላል፡፡

# <u>ክፍል ስምንት</u>

# <u>ብሄራዊ ደህንነት እና ተፈፃሚነት</u>

## ፶፩. <u>ብሄራዊ ደህንነት</u>

2/ In developing its Universal Access objectives, the Authority shall seek to ensure that Communications Services are accessible to the largest number of users possible, particularly in rural and remote areas of Ethiopia.

3/ It is hereby established a Universal Access Fund that shall be used to support universal access to Communications Service in Ethiopia. The amounts and sources of income for the Universal Access Fund and its manner of administration shall be determined by the Regulation to be issued by the Council of Ministers.

## 50. <u>Consumer Protection</u>

1/ The Authority shall have the power to issue such Directives in order to ensure that the interests of consumers of Communications Services are protected.

2/ The Authority shall adopt such Directives issued as per Sub-Article (1) of this Article through stakeholder consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation.

3/ Without limiting the authority contained in Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall in particular require each Telecommunications Operator to establish a Code of Conduct that shall specify the rights of consumers, including the consumer's right to lodge a complaint with the Telecommunications Operator or with the Authority.

4/ The Authority shall approve each Telecommunications Operator's Code of Conduct by a written Decision that the Authority shall adopt through Stakeholder Consultation pursuant to Articles 35-38 of this Proclamation.

5/ The Authority may require a Telecommunications Operator to make such changes to its Code of Conduct, as the Authority found Stakeholder Consultation, concludes are necessary in order to protect the interests of consumers.

# <u>PART EIGHT</u>

# <u>NATIONAL SECURITY AND ENFORCEMENT</u>

## 51. <u>National Security</u>

https://chilot.me



፩/ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለደንበኞቻቸው የሚሰጡትን የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚሥጥራዊነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ሁሉ መፈፀም አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ከቴሌኮሙኒኬሽን ደንበኞች ጋር የተያያዙ መረጃዎች እንዲሰጠው ሲጠይቅ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ማንኛውም ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ያስተላለፈውን ማንኛውንም ሕጋዊ ትዕዛዝ ማክበር አለባቸው፡፡

፫/ የወንጀል ምርመራ ወይም የሀገር ደህንነት ምርመራ ለማካሄድ ለተፈቀደለት የመንግሥት አካል ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቴሌኮሙኒኬሽን ላይ ሕጋዊ ክትትል ማድረግ እንዲችል የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ኔትወርካቸውን ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህን በማይፈፅሙ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች ላይ ባለሥልጣኑ ቅጣት ሊጥል፣ የተሰጣቸውን ፈቃድ ሊሰርዝ ወይም ሊያግድ ይችላል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ብሔራዊ ደህንነትን ለመደገፍ ዓላማ የቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተሮች የደንበኞች መረጃ ቋት በተሟላ ሁኔታ መያዝ እንዲችሉ፣ የሲም ካርድ ምዝገባ እንዲያከናውኑ እና ባለሥልጣኑ ደንበኞችን በተመለከተ የሚፈልጋቸውን መረጃ በያዘ ሁኔታ ብሄራዊ የደንበኞች መረጃ እንዲያደራጁ ለመጠየቅ ሥልጣን አለው፡፡

## ፶፪. ሕግ ማስፈፀም

፩/ ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ማናቸውም መመሪያ፣ የፈቃድ ሁኔታዎች፣ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች ወይም ሌሎች የቁጥጥር ማዕቀፎች እንደ አስፈላጊነቱ ከህግ አስከባሪ አካላት ጋር በመተባበር ለማስፈፀም ሥልጣን አለው፡፡

1/ Telecommunications Operators shall take all reasonable steps to ensure the confidentiality of their customers' telecommunications service.

2/ Notwithstanding the requirement of Sub-Article (1) of this Article, Telecommunications Operators shall comply with all lawful orders of any Ethiopian court of competent jurisdiction to provide such information relating to a customer's Telecommunications as an Ethiopian court of competent jurisdiction shall, pursuant to the laws of Ethiopia, require.

3/ A Telecommunications Operator shall provide access to its Telecommunications Network to permit duly authorized agents of the Government of Ethiopia to carry out lawful surveillance of Telecommunications in the conduct of a criminal investigation or national security investigation in accordance with the terms stipulated by a court of competent jurisdiction. In the event of noncompliance, the Authority may impose penalties, revoke or suspend the license to provide services.

4/ The Authority shall have the power to require Telecommunications Operators to register all SIM cards and to establish a National Subscriber Registry that shall contain such information concerning subscribers as the Authority may require for the purpose of consolidating and harmonizing the database of subscribers of the Telecommunications Operators in order to promote national security.

## 52. Enforcement

1/ The Authority shall have the power to enforce the provisions of this Proclamation and of any Directive, license conditions, its Decisions or other instrument that it may issue pursuant to the provisions of this Proclamation, when appropriate, in collaboration with law enforcement authorities.

https://chilot.me


፪/ ባለሥልጣኑ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ማናቸውም መመሪያዎች፣ የፈቃድ ሁኔታዎች ወይም ሌሎች የቁጥጥር ማዕቀፎች መከበራቸውን የመቆጣጠር ሥልጣን አለው፡፡ ቁጥጥሩ የባለሥልጣኑን ሠራተኞች መደበኛ የሥራ እንቅስቃሴዎችን ወይም ፍላጎት ባለው ማንኛውም አካል የቀረበ መረጃ ወይም ቅሬታን መሰረት ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭-፴፰ የተመለከቱትን ግልፅ የአሰራር ሥርዓቶች መሰረት በማድረግ በማንኛውም ባለፈቃድ ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችን ለመዳኘት እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በአዋጁ መሠረት የተቀመጡ የፈቃድ ሁኔታዎች ወይም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ሌሎች መመሪያዎች መጣስን በመገምገም እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፡፡

፬/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በአዋጁ መሠረት የተቀመጡ የፈቃድ ሁኔታዎች ወይም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያወጣቸውን ሌሎች መመሪያዎች የጣሰ ማንኛውም ሰው ላይ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የገንዘብ ቅጣት ወይም ካሳ መክፈልን ሊያካትት ይችላል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃድ መሰረዝን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ቅጣቶችን ሊያካትት ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ የሚወሰዱት እርምጃዎች ተመጣጣኝ፣ አድልኦ የሌለበትና ግልፅ መሆን አለባቸው፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፭) የተደነገገው ቢኖርም ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች እና ሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣት የሚያስከትሉ የሕግ መተላለፍ ዓይነቶች እንዲሁም የቅጣት መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

2/ The Authority shall have the power to monitor compliance with the terms of this Proclamation and of any Directive, license, or other instrument that the Authority may issue pursuant to the provisions of this Proclamation. Such monitoring may consist of regular activities of the Authority's staff or may arise as a result of information or complaints submitted to Authority by any interested party.

3/ The Authority shall have authority, pursuant to a transparent procedure consistent with the terms of Articles 35-38 of this Proclamation, to adjudicate all complaints against any licensee and shall have authority to assess appropriate remedies for any violation of the terms of this Proclamation, of any license issued pursuant to this Proclamation, or other instrument that the Authority may issue pursuant to the terms of this Proclamation.

4/ Such remedies as the Authority may impose pursuant to the terms of this Article may include fines or restitution to be paid by any Person who violates the terms of this Proclamation, of any license issued pursuant to this Proclamation, or of any Directive or other instrument that the Authority may issue pursuant to the terms of this Proclamation.

5/ Such remedies that the Authority may impose also include other appropriate sanctions as well, , if necessary including revocation of a license; provided, however, that such remedies shall be proportionate, non-discriminatory, and transparent.

6/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (1) to (5) of this Article, the Council of Ministers shall issue a Regulation that determines the types of infractions that would result in license revocation, suspension and other administrative measures and stipulate the penalties and the amount of fines to be paid.

https://chilot.me



## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፫. ክልከላ

በቴሌኮሙኒኬሽን ኦፕሬተር ከተመደበ ሠራተኛ ወይም በባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውም ሰው የቴሌኮሙኒኬሽን መስመርን ማገናኘት ወይም ማለያየት የተከለከለ ነው፡፡ ክልከላው የራሱን የቤት መገልገያ መሳሪያዎች የሚያገናኝ ወይም የሚያለያይ ሰውን አይመለከትም፡፡

### ፶፬. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል

### ፶፭. የተሻሩ ሕጎች

የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፦

፩/ የቴሌኮሙኒኬሽን አዋጅ ቁጥር ፵፱/፲፱፻፹፱ (እንደተሻሻለ)፤

፪/ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፯/፲፱፻፺፩፤

፫/ የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፫/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፯ (፮)፤

፬/ የፌደራል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ፲፻፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፳(፩) (ሐ)፣ (ፐ)፣ (ከ)፣ (ኸ) እና (ወ)፤

### ፶፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፮ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## PART NINE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 53. Prohibitions

No person is authorized to connect or disconnect Telecommunication Lines except for authorized employees of a Telecommunications Operator or a person licensed to do so by the Authority. This prohibition does not apply to a person connecting or disconnecting his own customer premises equipment.

### 54. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

2/ The Authority shall issue Directives for implementation of this Proclamation and Regulations issued as per this Proclamation.

### 55. Repeal

The following are hereby repealed:

1/ The Telecommunications Proclamation No. 49/1996 (as amended);

2/ Telecommunications Services Council of Ministers Regulation No. 47/1999;

3/ Broadcasting Service Proclamation No. 533/2007 Article 7(6)

4) Paragraphs (c) (o), (q), (r), and (s) of Article 20 (1) of Proclamation No.1097/2018.

### 56. Effective Date

This Proclamation shall come in to force upon publication in the *Federal Negarit Gazette*.

**Done at Addis Abeba, on this 12th day of August, 2019.**

**SAHLE WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me